# ለወደፊቱ ትግል ማመላከቻ የምርጫ 97 አጭር ግምገማ

## *መንደርደሪያ*

ከየካቲት 66 አብዮት ወዲህ የህዝብን ፍላጎት ያንጸባረቀ እንቅስቃሴ ሲቀጣጠል፤ በግንቦት 97 ምርጫ ዙሪያ የተነሳው የመጀመሪያው ነው። ይህ እንቅስቃሴ ከየካቲቱ በተሻለ ደረጃ መድረሻውን ያወቀ እና መሪ ድርጅቶቹን ያዘገጀ ነበር፤ ማለት ይቻላል። ነገር ግን፤ ከዚህ እይታ በተጨማሪ በመሪ ድርጅቶቹ አካባቢ የነበረውን የቅድመ-ዝግጅት ጉድለት አብሮ ካላጤኑ ስለምርጫ 97ና ከእዚህ ምርጫ ጋር በተያያዙ ጉዳዮች ላይ ጥሩ ግንዛቤ መያዝ አይቻልም።

በአብዛኛው ህዝብ ዘንድ የነበረው እይታ ግልጽ ነበር። ወያኔ ዘረኛ፤ ሙሰኛ፤ አምባገነናዊ፣ ጸረ-ህዝብ እና ጸረ-ሃገር አካል ስለሆነ በምርጫ 97 ወቅት ቢቻል የምርጫ ካርድን ብቻ በመጠቀም ከስልጣን ማባረር፤ ካልተቻለ ደግሞ አስፈላጊውን መስዋእትነት ከፍሎ የመጨረሻውን ፍልሚያ መፋለም ነበር። እንደ እውነቱ ከሆነ ደግሞ፤ ከምርጫ 97 ቀደም ብሎ በቴሌቪዥን መስኮቶች በተቃዋሚዎች እና በወያኔ ሀይሎች መሀል ይደረጉ በነበሩ ክርክሮች ወቅት በተቃዋሚ ድርጅቶች መሪዎች በኩል ይሰጡ የነበሩ አስተያየቶችን ለተመለከተ፤ የዚህ አይነቱ የህዝብ አቋም የሚገርም አይሆንም።

የተቃዋሚ ደርጅቶች መሪዎች በተደጋጋሚ፤ የምርጫ 97ቱን የህዝብ ድምጽ ለማስከበር የሚያስፈልገውን ሁሉ እንደሚያደርጉ በልበ ሙሉነት መናገራቸው የብዙውን ተራ ሰው ልብ አማልሏል። ሁላችንም እንደምናውቀው ግን፤ ይህ ተስፋ በጽኑ ድርጅታዊ መሰረት ላይ የቆመ ስላልነበር፤ በምርጫ 97 ዙሪያ የተነሳው እንቅስቃሴ የምርጫውን ውጤት አሰርቆ ለጊዜው ሊታፈን ችሏል።

"ለጊዜው" የሚባልበት ምክንያት፤ የእንቅስቃሴው መንፈስ በህዝብ ፍላጎት ላይ የቆመ በመሆኑ፤ የተቃውሞ እንቅስቃሴ መሪዎች የመጀመሪያውን እንቅስቃሴ ድክመቶች አርመው እስከመጡ ድረስ፤ የወያኔ እመቃ ዘለቄታዊነት ሊኖረው ስለማይችል ነው። የዚህ ጽሁፍ አላማ፤ ይህንን የህዝብ ትግል ስኬታማ ለማድረግ የሚያስፈልገው አካሄድ ምን መምሰል እንዳለበት ለመወያያ የሚሆኑ መንደርደሪያ ሃሳቦችን ማቅረብ ነው። ይህም ቅልብጭ ባለ መልኩ በሚቀጥለው የዚህ ጽሁፍ ክፍል ውስጥ የሚቀርበው ነው።

በቅድሚያ ግን፤ ትግሉን ስኬታማ ለማድረግ በሚል እምነት ለመንደርደሪያነት የምናቀርባቸውን ሃሳቦች እንድንሰነዝር ባስገደዱን ጉዳዮች ላይ እናተኩራለን። ከእነዚህ ጉዳዮች መሃከል በተለይ ከላይ "ድክመቶች"[1] ብለን የጠቆምናቸውን በጥልቀት ለመቃኘት እንሞክራለን። ይህ ቅኝት በብቃት ሊከናወን የሚችለው ግን፤ ድክመቶቹ በተነሱበት ነባራዊና ተጨባጭ ሁኔታ ውስጥ በአግባቡ አስቀምጠን መገምገም ስንችል ነው። ለዚህም ሲባል፤ በመጀመሪያ ስለ ምርጫ 97 እንቅስቃሴ አነሳስ ጥሩ ጭብጥ ሊኖረን ይገባል።

## 1-ምርጫ 97ና የወቅቱ ነባራዊና ተጨባጭ ሁኔታዎች

የምርጫ 97 ማስገምገም እና ከርሱም የተከተሉት ሁኔታዎች የዚያን ታላቅ ታሪካዊ ሁነት ዋነኛ ተዋናዮች ሁሉ ከጠበቁት በላይ በመሄድ ያስደነገጠ ነበር። እነኝህ ተዋናዮች በስም ሲጠሩ፤ ህዝቡ፤ ተቃዋሚ ድርጅቶች፤ የወያኔ መንግስት፣  ደጋፊዎቹ እና የውጭ ምእራባዊ መንግስታት (በተለይ የአሜሪካ መንግስት) ናቸው። ለተዋናዮቹ ሁሉ ድንጋጤ ምክንያቱ ደግሞ፤ እያንዳንዳቸው ስለ ምርጫ 97 ታሪካዊ ክስተትነት የነበራቸው እይታ ውሱንና ፈጽሞ ከእውነታው ጋር ያልተመጣጠነ መሆኑ ነበር። ከምእራባውያን እንጀምር።

### *የምእራባውያን እይታ*

በውጭ መንግስታት በኩል፤ ከተወሰነ ወቅት ወዲህ በአለማችን ውስጥ (በተለይ በአፍሪካ) የመልካም አስተዳደር እና የዴሞክራሲያዊ ስርአት መስፋፋትን ለማበረታታት የተያዘ አቅጣጫ አለ። ምእራባውያኑ

---

[1] በነገራችን ላይ ‹ድክመቶች› እያልን በዚህ ጽሁፍ ውስጥ የምንጠቀማቸውን ጉዳዮች፤ በተለምዶአዊ አማርኛ ስሜቱ ለወቀሳ መንደርደሪያ እድርገን ከመውሰድ መታቀብ እንዳለብን ማስታወስ እንወድዳለን። ከዚያ ይልቅ፤ በአዎንታዊ የግምገማ ስሜቱ ለወደፊት ለሚነደፍ የተግባር እንቅስቃሴ መንደርደሪያ የሚሆን የተለምዶ መድበል ተደርጎ ሊወሰድ ይገባል።

ይህንን አቅጣጫ የያዙት በተለያዩ ጂኦ-ፖለቲካዊ፣ ሰብአዊ፣ ፖለቲካዊ እና ኤኮኖሚያዊ ምክንያቶች የተነሳ ነው፡፡ እኒህ ምክንያቶች ተለያይተው በዘፈቀደ የተቀመጡ ቢመስሉም እርስ በርሳቸው ውስብስብ በሆኑ ገመዶች የተቆላለፉ ናቸው፡፡ የምክንያቶቹን ውስብስብነት ለመረዳትም ሆነ፣ እያንዳንዳቸውን የተናጠል ክብደት በሚገባ ለመመዘን ሁሉንም ተራ በተራ እያነሳን በመጠኑም ቢሆን መቃኘት ይኖርብናል፡፡

***ጂኦ-ፖለቲካዊ ስሌቶች***

ሶቪዬት ህብረት ከወደቀበት ከ1990 ወዲህ አለማችን አሜሪካ እና ምእራባዊ አጋሮቿ እንደልባቸው የሚናኙባት አሀዳዊ ዋልታ ሁናለች፡፡ ከዚህ አሀዳዊ ዋልታ መፈጠር ጎን ግን፣ የምእራብ ሃገሮችን የዘለቄታ የበላይነት የሚፈታተኑ ሁነቶችም ተፈጥረዋል፡፡ ከእነዚህ ውስጥ ዋነኛው የቻይና መነሳት ነው፡፡

ቻይና ሩብ የሚሆነው የአለም ህዝብ የሚኖርባት ሀገር ብትሆንም፣ ከ15 አመታት በፊት እዚህ ግባ የሚባል የኤኮኖሚ አቅም ያልነበራት ሀገር ነበረች፡፡ ከማኦ ዜ ዱንግ ሞት በመቀጠል የመጣው ለውጥ ግን፣ ለተከታታይ ብዙ አመታት የሁለት አሃዞች ኤኮኖሚ እድገት እያስመዘገበች እንድትሄድ በማስቻል፣ በአሁኑ ወቅት የአለማችን አራተኛው ታላቅ ኤኮኖሚን የያዘች ሀገር አድርጓታል፡፡ ከዚህም ጋር ተያይዞ ፖለቲካዊ እና ወታደራዊ ተጽእኖዋ አይሏል፡፡

የቻይና በዚህ አይነት ደረጃ በአለም መድረክ ላይ ብቅ ማለት ለብዙ አመታት ረግቶ የኖረውን ምእራባውያኑ እንደሚሉት "አለማቀፋዊ ስርአት" (world order) እያናጋው ይገኛል፡፡ በቀደሙት አመታት፣ የአሜሪካን ቁጣ እየፈራ የታዘዘውን የሚፈጽም አምባገነን ሁሉ፣ ቢያንስ ለማስፈራሪያነት "ቻይናን መጎብኘትን" ዘዴ ብሎ ይዞታል፡፡ ካስቸገራችሁኝ ቸይና ላይ ሄጄ እለጠፋለሁ የሚል ማስፈራሪያ ለምእራባውያኖቹ በተዘዋዋሪ ማስተላለፍ መሆኑ ነው፡፡ ቻይናም በበኩሏ፣ በከፍተኛ ፍጥነት እያደገ ለሚገኘው ኤኮኖሚዋ ጥሬ ሀብት ፍለጋ በምንም ሞራላዊ ግዴታ ያልታቀበ ግንኙነትን ፈቃደኛ ከሆኑ ሃገሮች ጋር ሁሉ እየዘረጋች ትገኛለች፡፡ በቻይና እቃዎችን ለማምረት የሚወጣው የጉልበት ዋጋ ከምእራብ ሀገሮች ጋር ሲወዳደር በጣም ዝቅተኛ በመሆኑ፣ የቻይና የእቃ ምርቶች የድሀ ሀገሮችን ብቻ ሳይሆን የአውሮፓ እና የአሜሪካ ገበያዎችን ሁሉ እያጥለቀለቀ ነው፡፡ ቻይና የኤኮኖሚ ጥቅሟን ለመጠበቅ ስትል፣ በተባበሩት መንግስታት ድርጅት( ተ.መ.ድ ) ውስጥ ያላትን የቪቶ ሀይልም (veto power) ከእዚህ ቀደም ተጠቅማበት ከምታውቅበት አግባብ ውጭ መጠቀም ጀምራለች፡፡

እንግዲህ ይሁ ሁሉ፣ የመጪው ጊዜያትን ምንነት ጠቋሚ እንጂ መጨረሻው አይደለም፡፡ እንደ እውነቱ ከሆነ ደግሞ፣ ይህ እስካሁን የታየው "አለማቀፋዊ ስርአት" መናጋት፣ ቢያንስ በሚቀጥሉት አመታት ውስጥ የሚባባስ እንጂ የሚበርድ አይሆንም፡፡ ቢያንስ፣ መካከለኛው ምስራቅ አካባቢ ያሉ አወዛጋቢ እና ሌሎች ተመሳሳይ ጉዳዮችን ትተን፣ በፑቲን አመራር የሩሲያ መነሳት፣ ሩሲያ ከኔቶ ጋር ያለው ውዝግብ፣ የህንድ ኤኮኖሚ ግስጋሴ፣ የተመድ ጸጥታ ኮሚሽን ቋሚ አባላትን የመጨመር አጀንዳ፣ ብዙ የደቡብ አሜሪካ እና የእስያ ሀገሮች ከቅርብ ጊዜ ወዲህ የተጣደፈ ኤኮኖሚ እድገት የማስመዝገባቸው ሁኔታ የተጀመረውን "አለማቀፋዊ ስርአት" መናጋት ይበልጥ የሚያወሳስቡ እና የሚያደበላልቁ ጉዳዮች ናቸው፡፡ መጪውን የሚያውቅ እግዚአብሄር ብቻ ነው ብለን ብናምን እንኳን፣ እውነታው የአለም ማእከል ከምእራብ እየተከፈለ ወደ እስያ እየዞረ መሆኑ፣ ግልጽ ሆኗል፡፡

አለማቀፋዊው ስርአት በዚህ አይነት መልክ መለወጡ ሁሉንም የአለም ክፍል የሚመለከት ጉዳይ ነው፡፡ በመሆኑም፣ ካልታደሉት አንዳንድ የአፍሪካና ሌሎች ሀገሮች በስተቀር፣ የተቀሩት ሃገራት የማይቀረው የስርአት መናጋት በሚፈጠረው ሁኔታ ጥቅማቸው እንዳይሸረሸር ወይም ጥቅማቸውን ለማስፋት ሲጥሩ ይታያሉ፡፡ በአሁኑ ወቅት የምእራባውያን ሀገሮች ዋነኛ ትኩረት ያነጣጠረው እየተፈጠረ ያለው አዲስ አለማቀፋዊ ሁኔታ የሚያስከትልባቸውን ጉዳቶች በተቻለ መጠን ሁሉ ለማሳነስ የሚቻልባቸውን ስልቶች በመቀየስ ላይ ነው፡፡

እነዚህ ስልቶች በአብዛኛው፣ አለማቀፋዊ ኤኮኖሚያዊ፣ ፖለቲካዊ፣ ህጋዊ እና ሰብአዊ ተቋማትን በማደራጀት እና በማዋቀር ዙሪያ የሚጠነጠኑ ቢሆኑም፣ በአሜሪካ በኩል ግን ከዚህም አልፎ ወታደራዊ ጀብድንም ያካተተ

እንደሚሆን ግልጽ ሆኗል። በአሜሪካ በኩል ጉልበትንም ጨምሮ የመንዝ ጽንፈኛ አቅጣጫ የተከሰተው በሁለት ምክንያቶች ነው። አሜሪካ በአለማችን ውስጥ ያለችው ብቸኛ ወታደራዊ ልእለ ሃያል በመሆኗ እና በአሁኑ የቡሽ አስተዳደር ውስጥ ኒኦ ኮንሰርቫቲቭ ሊበራልስ በመባል የሚታወቁት ጽንፈኛ የቀኝ አክራሪ ሀይሎች የአሜሪካን መንግስት ፖሊሲዎች በመቅረጽ ከፍተኛ ተጽእኖ ማድረግ የሚችሉበት ስልጣን መያዛቸው ነው።

እንደ እነዚህ ጽንፈኞች እምነት[2]፣

1. አሜሪካ በአሁኑ ወቅት ብቸኛዋ ልእለ ሃያል መንግስት ስለሆነች፣ ማንኛውንም መንገድ ተጠቅማ (ወታደራዊ ጉልበቷን፣ የኤኮኖሚ አቅሟን እና በአለም አቀፋዊ ድርጅቶች ውስጥ ያላትን ተጽእኖ) አለምን በምስሏ መቅረጽ አለባት፣
2. ይህንን አላማ ለመፈጸም ደግሞ፣ወታደራዊ ጉልበት አስፈላጊ ሊሆን ስለሚችል፣ ወታደራዊ ቁመናዋ ማንም ሀገር ሊጋፈጠው ቀርቶ ለመጋፈጥ ሊያስበው ከሚችለው በላይ መዳበር ያስፈልገዋል።

ይህ ፖሊሲ በፖለቲካ መልኩ በአፍሪካ ላይ በስራ የተተረጎመው በተለያየ ማጭበርበሪያ ዘዴዎች ስልጣን ላይ ተፈናጥጠው የሚገኙ አምባገነኖችን ነጻ እና ፍትሃዊ ምርጫ እንዲያካሂዱ በመግፋት ነበር። ጎረቤታችን ኬንያን ለብዙ ዘመናት በማጭበርበር የምርጫ ውጤቶች ከለላ ሲገዛ የኖረው የአራፕ ሞይ መንግስት እንዲያበቃ የቻለበት አንዱ ምክንያት፣ ከዚህ ፖሊሲ የተከተለው ተጽእኖ ጠንካራነት ነበር። በእኛም ሀገር ከ97 በፊት ታይቶ በማይታወቅ ሁኔታ ወያኔ ነጻ ምርጫ ለማካሄድ የተገደደበትም አንዱ ወሳኝ ሁኔታም ይኸው ነበር።

*__ሰብአዊ፣ ፖለቲካዊ እና ኤኮኖሚያዊ ስሌቶች__*

የሰው ልጅ በሳይንስ እና ቴክኖሎጂ ተራቅቆ ቀደም ባሉት ዘመናት ሊታለሙ የማይችሉ ስርቻዎችን ሁሉ እየጎረጎ ባለበት ዘመን ውስጥ፣ ለአብዛኛው ህዝቧ የምድር ገሀነም ሁና ልትታይ የሚገባት አፍሪካ የምትባል አህጉር አለች። በአፍሪካ፣ በቀላል የህጻናት ጤና አጠባበቅ ጉድለት ምክንያት፣ ገና በለጋነታቸው የሚቀሰፉ ህጻናት ቁጥር እጅግ ብዙ ነው። ቀላል ህክምናን ባለማግኘት፣ በረሀብ፣ በእርስ በርስ ሰው ሰራሽ ጦርነት ምክንያት የሚያልቀው አፍሪካዊ ጥቁር ዜጋ ከብዛቱ የተነሳ ይህ ነው የማይባል ነው። በአንጻሩ፣ በአውሮፓ እና አሜሪካ ሀብታሞች ደረጃ እንኳን ቢለካ በከፍተኛ የቅንጦት ደረጃ ላይ በሚመደብ የተንደላቀቀ ህይወት የሚኖሩ እፍኝ የማይሞሉ የፖለቲካ ባለስልጣኖች እና ጥገኞቻቸው በአፍሪካ ምድር እናገኛለን። አፍሪካ እነዚህ ጥቂት ደልቃቆች ገደብ የለሽ መብት እና ስልጣን ያካበቱባት አህጉር ሁና ቆይታለች።

ዛሬ በአፍሪቃ የሰፈነው አሳዛኝ እና ቀፋፊ ሁኔታ፣ በአለም አቀፍ ዘመናዊ የመገኛኛ-ብዙሃን አድገት የተነሳ መላው የሰው ዘር የሚያውቀው ጉዳይ ሆኗል። ለአብዛኛውም ሰብአዊ ፍጥረት የህሊና ቁስል መሆን ጀምሯል። ከፊሉ ምንም ማድረግ ባለመቻሉ ሰምቶ በማለፍ፣ ሌላው ደግሞ በየግሉ የአቅሙን ያህል ለእርዳታ ድርጅቶች የአቅሙን እያዋጣ ችግሩን ለመታገል ሲሞክር ይታያል። በኑሮው አደረጃጀት ምክንያት የአፍሪካን ጣርና በደል ከመስማት ተከልሎ ይኖር የነበረው ሁሉ፣ ከቅርብ ጊዜ ወዲህ ይህንን ስቃይ ለመቀነስ ትላልቅ አስተዋጽኦዎችን ለማበርከት ጥረት ሲያደርግ ይታያል። ለዚህ ለውጥ ተመስጋኙ ብዙ ቢሆንም፣ ይህንን የአፍሪካ ችግር ለአለም ለማስተዋወቅ በሙሉ ትጋት ሲንቀሳቀሱ የኖሩ ሰብአዊነት የተላበሱ የታወቁ ግለሰቦች፣ አብያተ ክርስቲያናት፣ የሰው ልጆች መብት ተከራካሪ እና የግብረ ሰናይ ድርጅቶች እንዲሁም ሌሎችም ተቀዳሚውን ስፍራ ይይዛሉ። ይህ ጥረት ካለፉት አስርተ-አመታት ወዲህ፣ በከፊል በአውሮፓ ግራ ዘመም መንግስታት በብዛት መምጣታቸውን ተከትሎ፣ የሚዲያዎችን እና የመንግስታት መሪዎችን ጆሮ ሊያገኝ በቅቷል።

ከዚህም በመቀጠል፣ በአሜሪካ እና በዩናይትድ ኪንግደም ወደስልጣን የመጡት የክሊንተን እና የብሌር መንግስታት የአፍሪካ ብሶት የአለም መንግስታትን ጆሮ እንዲያገኝ ከፍተኛ ጥረት አድርገዋል። የአፍሪካ ብሶት

[2] ኢራቅ የዚህ ፖሊሲ መፈተሽ የሆነችው የመጀመሪያ ሜዳ ነች። የአሜሪካ ወታደራዊ ጀብድ ኢራቅ ውስጥ ተቀርቅሮ ቀረ እንጂ፣ ያ ፍተሸ ውጤት ቢያስገኝ ኑሮ ቻይና እንኳን ብትቀር፣ ሲሪያ፣ ኢራን እና ሰሜን ኮሪያ ተከታይ ሊሆኑ ይችሉ እንደነበር የሚያሳዩ ፍንጮችን ካለፉ የፕሬዚዴንት ቡሽ ንግግሮች በማጣቀስ መመልከት ይቻላል።

የመንግስታት መሪዎችን ትኩረት ማግኘቱ፤ ችግሩን ከመሰረቱ ለመቅረፍ የሚቻልበትን መንገድ ከፍቷል። በተለይ፤ የአፍሪካ ሀገሮች የመልካም አስተዳደር፤ የግልጽነት እና የተጠያቂነት ስርአትን ምስረታ ካላካተቱ ችግሮቻቸው በኤኮኖሚ ርዳታ ብቻ ሊፈቱ እንደማይችሉ አጠቃላይ ተቀባይነት መገኘቱ፤ እስካሁን ድረስ የተገኘው የዚህ ጥረት ተጨባጭ ድል ነው።

ይህንን ጥረት በትጋት ይገፋ የነበረው እንግሊዝ የአውሮፓ ህብረት ሰብሳቢ በነበረችበት ወቅት ስለነበር፤ አሁን ሁኔታው ለጊዜው የቀዘቀዘ ይመስላል። ይህ የመቀዝቀዝ ሁኔታ ግን ዘለቄታዊነት እንደማይኖረው ተስፋ ሰጪ ምልክቶች አሉ። አንዱ፤ ጎርደን ብራውን ቀጣዩ የእንግሊዝ ጠቅላይ ሚኒስቴር መሆናቸው ነው። ለዚህ አጀንዳ መገፋት ከላይ የገለጽነው ሰብአዊ እይታ የማይናቅ ስፍራ ቢኖረውም፤ ዋናው ምክንያት ግን፤ ይህንን እይታ ቀደም ብለን ከዘረዘርነው አለማቀፋዊ ስርአት መዘበራረቅ ጋር የሚያያይዝ የምእራብ ሀገሮች ኤኮኖሚያዊ እና ፖለቲካዊ ጥቅሞች ስላሉበት መሆኑን ግን መሳት አይገባንም።

አፍሪካ ወደ 1 ቢሊዮን የሚጠጋ ህዝብ የሚኖርበት አህጉር ነው። በአሁኑ አለም ውስጥ፤ ሁሉም በየአካባቢው የኢኮኖሚ ቀጣናውን እየለየ ሲገኝ፤ ይህ አህጉር ብቻ ለማንም መፈንጫ ተመቻችቶ የተቀመጠ ነው። በሌላ ገጽታው ደግሞ፤ ከአውሮፓውያን ጋር ከቅኝ ግዛት ዘመን ጀምሮ፤ ከአሜሪካ ጋር ደግሞ ከሁለተኛው የአለም ጦርነት ወዲህ፤ በተለያዩ ሰርጦች ማለትም የፋይናንስ፤ ኢንሹራንስ፤ ኮንሰልታንሲ፤ ትምህርታዊ፤ ቴክኖሎጂያዊ፤ ወታደራዊ እና ተመሳሳይ በሆኑ ዘርፎች ተቆላልፎ ይገኛል። በመሆኑም፤ አፍሪካን መፈንጫ አድርገው ሊጋልቡት ከሚችሉ ከሌሎች ሀይሎች ይልቅ አህጉሩ ለምእራባውያን የተመቻቸ መሆኑ በምእራቡ ፖለቲከኞች ዘንድ የሚታወቅ ነው።

ለአፍሪካ ህዝቦች ርዳታን መለገስ የተረጂውን ኤኮኖሚያዊ አቅም በማጎልበትና ሽቀጥ የመሸመት አቅሙንም የሚጨምርለት ብቻ ሳይሆን[3]፤ ተረጂውን ለረጂው ተጽእኖ የሚያመቻችም ጭምር ነው። የተረጂው ህብረተሰብ የተለያዩ ተቋማት ከረጂው ማህበረሰብ ጋር በጠበቁ ገመዶች ቢተሳሰሩ ደግሞ፤ ይህ ተጽእኖ ዘለቄታዊነት ይኖረዋል። ከዚህ በተጨማሪ ደግሞ፤ ይህ ትስስር ማንም አጉራ ዘለል አምባገነን ባሻው ወቅት በገዛ ህዝቡ ኪሳራ እንዳይበጣጥሰው የሚደረግ ቢሆን ትስስሩ የበለጠ አስተማማኝ ይሆናል። መልካም አስተዳደር፤ ግልጽነት እና ተጠያቂነትን ያካተተ የመንግስት ስርአት ደግሞ፤ ይህንን ለማሟላት የሚያስችል አቅም አለው።

ለምእራባውያን፤ ይህ ተግባር ባብዛኛው የሚጠይቀው ባለው ላይ መገንባትን እንጂ፤ እንደ አዲስ መጀመርን አይሆንም። ከዚህ በተጨማሪ ደግሞ፤ ለዚህ ቁርኝት ማስተማመኛነት ከላይ ለተጠቀሰው የመልካም አስተዳደር ስርአት ምእራባውያን ሀገሮች የሚሰጡት ድጋፍ፤ የተረጂውን ሀገር ተራ ህዝቦች ከበሬታ እና አመኔታ ሊያስገኝ የሚችል የሞራል ሀይል ነው።

እንግዲህ፤ በምርጫ 97 ዙሪያ የነበረውን የምእራብ ሀገሮች እይታ እንደሚቀጥለው ማጠቃለል እንችላለን።

- ምርጫው ነጻ እና ፍትሀዊ እንዲሆን በወያኔ መንግስት ላይ ተጽእኖ አድርገዋል፤
- ምርጫው ግልጽ እና ፍትሀዊ በሆነ መንገድ ቢጠናቀቅ ቅን ፍላጎት ነበራቸው።

***<u>የወያኔ እይታ</u>***

በምርጫ 97 ዙሪያ የነበረው የወያኔ እይታ በጥቅሉ ሲቀመጥ፤ ከቅን ስህተት የተከተለ የሚመስል የማጭበርበሪያ ስልትን በመጠቀም ምርጫውን ወያኔ እንዲያሸንፈው ማድረግ ይቻላል የሚል ነበር። ለዚህም ትልም ዋነኛ ታሳቢዎች የሚከተሉት ነበሩ።

1. ከምእራባውያን የመጣውን ነጻ ምርጫ የማካሄድ ተጽእኖን ማስተናገድ አስፈላጊነት መገንዘብ፤

---

[3] በሁለቱ ህብረተሰቦች መሀል የሚኖረው ተቋማዊ ( institutional ) መስተሳሰር የሃገራትን የገበያ ምርጫ ነጻነት ጭምር በተወሰነ ደረጃ የመገድብ ነው።

2. በተቃዋሚ ድርጅቶች አካባቢ ያለው ክፍፍል እና ዝርክርክነት፤ በነጻ ምርጫ አብላጫ ድምፅን እንዲያገኙ አያስችላቸውም የሚል ግምት፤
3. በመላው ሃገሪቱ የሚገኙ የአገዛዙ አስተዳደራዊ መዋቅር ወኪሎች ጥቅም ከኢህአደግ በስልጣን መሰንበት ጋር የተቆራኘ መሆኑን ስለሚያውቁ ያለምንም ጉትጎታና ማበረታት ማንኛውንም ዘዴና ስልት በመጠቀም ተቃዋሚዎች በየአካባቢው አብዛኛው ድምጽ እንዳያገኙ ማድረግ ይችላሉ የሚል እምነት
4. ስለራስ ጥንካሬ የተወሰደ የተሳሳተ ግምት፤ ናቸው።

በተራ ቁጥር 1 በተቀመጠው ጉዳይ ላይ ቀደም ብለን ያተትንበት ስለሆነ፤ ወደርሱ አንመለስም። በተራ ቁጥር 2 ስለተቀመጠው ጉዳይ ደግሞ፤ የተቃዋሚ ድርጅቶችን እይታ በምንቃኝበት ወቅት በሰፊው ስለምናትትበት፤ በርሱም ላይ ይህንን ያህል ጭብጥ ከያዝን ለጊዜው በቂ ነው። በተራ ቁጥር 3 እና 4 ስለተቀመጡት ጉዳዮች ግን፤ በጥቂቱ ልንተችበት እንወድዳለን።

በተራ 3 ላይ የተቀመጠው ጉዳይ ላይ የወያኔ አቋም በአንድ በኩል በድምጽ እንዳይሸነፍ በሌላ በኩል ግን "ነጻና ፍትሃዊ ምርጫ አድርጊያለሁ" በማለት በአለም አቀፍ ማህበረሰቡ ፊት እንዲያቅራራ የሚያስችለውን ተደራራቢ የአደጋ መከላከያዎችን በውስጡ የገነባ ነበር። በሃገር ውስጥ ላሉት መንግስታዊ ተቋማት ውስጥ ለሚሰሩ ሰራተኞች፣ ለመንግስት ሲቪል ሰራተኛው፣ ለወታደሩ፣ለፖሊሱ፣ ለሌሎችም እና እንዲሁም ለራሱ ካድሬዎች ሳይቀር ምርጫውን በሚመለከት የስነ ምግባር መመሪያ ያስተላልፋል። ምርጫውን ነጻና ፍትሃዊ ለማድረግ ቆርጦ መነሳቱን ይገልጻል። የእዚህን መመሪያና መግለጫ ቅጅ ለአለም-አቀፍ ህብረተሰቡና ለተቃዋሚ ድርጅቶች ያስተላልፋል። በሌላ በኩል ግን በተራ ቁጥር 3 በተቀመጠው ስሌቱ መሰረት የራሱ መንግስት ተቋማት ሰራተኞች ጥቅማቸውንና ህልውናቸውን ለማስከበር ተቃዋሚ ፓርቲ ተወካዮችን አስፈላጊ ሆኖ ካገኙት ከመግደል፣ ከማሰር፣ ከማፈናቀል እንደማይመለሱ ያውቀል። እነዚህ መንግስታዊ አካላት በምርጫውና በድምጽ ቆጠራው ወቅትም ኢህአዴግን አሸናፊ አድርገው ለማውጣት የማይፈነቅሉት ክፋት እና የማይፈጽሙት ወንጀል እንደማይኖር ኢህአዴግ አስቀድሞ ያሰበበት ነበር። እንዲህ አይነት በደልና ግፍ በተቃወሚዎች ላይ ቢፈጸም አቤት የሚባልባቸው አስተዳደራዊ ተቋማት፣ የምርጫ ቦርድና የፍትህ ተቋማትም በወያኔ የጥቅም ጀሌዎች የተሞሉ በመሆናቸው ሌላው የሽንፈት መከላከያ መሳሪያ ተደርገው ተወስደዋል። ለተቃዋሚው አቤቱታ ምላሻቸው መንግስትን የሚያጋለጥ ውሳኔ እንደማይሆን ወያኔ ጠንቅቆ ይታወቃል። ይህንን ሁሉ አልፎ ለሚመጣ ነገር ደግሞ ኢህአዴግ ባምሳሉ **የፈጠረውን** የጦር፣ የፖሊስና የጸጥታ ሃይል በህዝብ ላይ ለማዝመት ሳንጃውን ወድሮ ቆሟል። ኢህአዴግ ወደ ምርጫው የገባው ይህንን ሁሉ ተማምኖ ነበር። በሂደት የተረጋገጠውም ይህ ነው። ኢህዴግን በስልጣን እንዲሰነብት ያስቻለው ሁሉንም መንግስታዊ ተቋማት በቁጥጥሩ ስር በማድረግ አደጋ በሸተተው ቁጥር እነዚህን መንግስታዊ ተቋማት እንደ አስፈላጊነቱ የፖለቲካ ተቀናቃኞቹንና ደጋፊዎቻቸውን ለመምታት በመቻሉ ነው። እነዚህን ተቋማት ከማንኛውም የፖለቲካ ድርጅት ነጻ ሆነው እንዲዋቀሩ የቀረበለትን ወደፊትም የሚቀርብለትን ሃሳብ የማይቀበለውም፣ የስልጣን ዋስትናው እነዚህን ተቋማት እንዳሻው ማዘዝ እና መጠቀም ብቻ መሆኑን ስለሚያውቅ ነው።

ወደ ተራ ቁጥር 4 ስንመለስ የሚከተለውን ማለት እንችላለን። የወያኔ መሪዎች ከእውነታ ርቀው የሚኖሩበት የቤተምንግስት በድሎት የተሞላ ሕይወት የተለመደውን የገዢ መደብ ስነልቦና እንዳላበሳቸው ግልጽ ነው። ይህ አደገኛ የገዥ መደብ ህሊናቸው ደግሞ ስለራሳቸው ብዙ የተሳሳቱ ግምቶች እንዲኖራቸው አድርጓቸዋል። በወያኔ እይታ፤ ከ "ትምክህተኛ አማሮች" በስተቀር ኢህአዴግ የኢትዮጵያ ህዝቦች ሁሉ አለኝታ ነው። የገጠሩ ህዝብ በአብዛኛው የስርአቱ ተጠቃሚ ነው። ጭቁን ብሄረሰቦች በሙሉ ነጻ የወጡት በወያኔ እንቅስቃሴ መሪነት በመሆኑ፤ ከአማራው በስተቀር አብዛኛው ቀሪው የኢትዮጵያ ህዝብ ሁሉ ከተቃዋሚዎቹ ይልቅ ወያኔን ይመርጣል። ከአማራ ውጭ የሚገኙ አንዳንድ ብሄረተኛ እንቅስቃሴዎች በዚህ ምርጫ ወቅት የሚያሰጉ አይደሉም። ምክንያቱም የህዝቦቻቸው ድጋፍ ያሏቸው ኦነግን እና ኦብነግን የመሳሰሉት ብሄረተኛ

እንቅስቃሴዎች በህጋዊነት ከለላ ከምርጫ ውጭ እንዲሆኑ ተደርገዋል። በተለያየ መልካቸው የሚቀርቡ ቢኖሩ ደግሞ፤ የወያኔ ተለጣፊ የሆኑት ድርጅቶች በአስተማማኝ[4] ሁኔታ ያሸንፏቸዋል።

ከዚህ ሁሉ ከተረፈው፤ በከተሞች ነዋሪ ከሆነውም ህዝብ መሀል ቢሆን፤ ወያኔን አምርረው የሚጠሉት "ትምክህተኛ አማሮች" ብቻ ናቸው። "ትምክህተኞቹ" ደግሞ በተለያዩ ድርጅታዊ ጎራዎች የተከፋፈሉ ናቸው። በመሆኑም ይህ ክፍፍላቸው በምርጫው ወቅት የሚያገኙትን ድምጽ ይከፋፍለዋል። በእዚህም የተነሳ አንዳቸውም ኢህአዴግ ከሚያገኘው ደምጽ በላይ ማግኘት አይችሉም። አዲስ አበባን በተመለከተ አደጋ ሊኖር ቢችልም፤ አስተዳደሩን ሽባ የሚያደርጉ ድንጋጌዎችን በወጪው ፓርላማ መሳሪያነት ከወዲሁ አዘጋጅቶ መቀመጥ ይቻላል። በመሆኑም፤ በዚህ ምርጫ ውስጥ በነጻ መሳተፍ ከምእራባውያን ጋር በመፋጠጥ ለከተለው የሚችለውን ጉዳት ያሰወግዳል። እንዲያውም ከፍተኛ ጠቀሜታ ያስገኛል።

እርግጥ ነው ወያኔን በቅጡ ለተረዳው የወያኔ ደመ-ነፍስ ይህንን የመሰለ ቁማር ለመጫወት የሚከጅል አልነበረም። በወቅቱ ከመሪዎቹ መሀል ይህንን አካሄድ የተጠራጠሩ እንደነበሩ መገመት አዳጋች አይሆንም። የመለስ ዜናዊ እብደት ቀመስ ባህርይ ቁማሩን ለመጫወትና ለማሸነፍ የሚያስችል ዘዴዎች በእጃችን አሉ ብሎ ስላመነ በምርጫ የመሄዱን አቅጣጫ እንዲገፋበት አድርጎቷል። መለስ ከምርጫው በኋላ ስለምርጫው ሲናገር "የተቀመረ ስሌት (calculated risk) ወሰድን፣ ፊታችን ላይ ፈነዳ" ማለቱ ለወያኔ፣ በተለይ ለመለስ ዜናዊ ምርጫው ቁማር እንደነበር የሚያሳይ ነው። መለስን ለእዚህ በእብደት የተሞላ ቁማር ውስጥ የዶለው የራሱ ምክንያቶች አሉት። መለስ ዜናዊ በወያኔ እንቅስቃሴ ውስጥ የነበሩትን አንጋፋ ጓደኞቹን ፈንግሎ የፈላጭ ቆራጭነት ስፍራን ከያዘ በኋላ፤ በሀገሪቱ ውስጥ ተቀናቃኝ የሌለው ብቸኛ መሪ ለመሆን ብዙ ነገሮችን ቀይሶ ነበር። ከእነዚህም መሀል አንዱ፤ ከአለም ታላላቅ የፖለቲካ ሰዎች መሀል የሚቆጠር መሆኑን በዙሪያው ለተሰበሰቡት የኢህአዴግ ደናቁርት ማሳየት ነበር። ይህ ፍላጎት ከፖለቲካ ስሌት ብቻ የመነጨ ሳይሆን፤ መለስ ዜናዊን እንደ አሻንጉሊት ከሚጫወትበት ገደብ የለሽ ስለራሱና ስለማንነቱ ከነበረው የተጋነነ ግንዘቤ (inflated ego) ጋር የተቆራኘ ነበር።

ከዚህም ተነሳ ከዚያ ግን፤ መለስ ዜናዊ ከአለም ታላላቅ የፖለቲካ ሰዎች ተርታ ለመቆጠር ሲል አጎብድዶ የበርካታ መንግስታት መሪዎችን ጫማ ስሟል። በየሳምንቱ የውጭ ሀገር ጉብኝት ነበር። አንድያውን ይህን ሰው ወደ እብደት ሊነዳው ደግሞ፤ በተሳሳተ ምክር ተነስቶ የእንግሊዙ ቶኒ ብሌር የአፍሪካ ኮሚሽን አባል አድርጎ ከመረጠው በኋላማ፤ የምእራብ ሀገር ሚዲያዎችን ትኩረትም ለማግኘት ሞክሯል።[5] ይህ ሁሉ ሲደራረብ ኢህአዴግ በሚባለው ጥርቃሞ ውስጥ መሪዎች ተብለው የተሰየሙት ደናቁርት፤ መለስ ዜናዊን እንደ ምድራዊ አምላካቸው አድርገው የወሰዱበት ሁኔታ በየእለቱ ሲጠነክር ተስተውሏል። ታዲያ የዚህ ሁሉ መቋጫ፤ የመለስ ዜናዊ ነፍስ፤ ፈረንጆች ‹የዘውዱ እንቁ› ወይም ‹የኬኩ ጌጥ› እንደሚሉት ሁሉ፤ በ‹ዲሞክራሲያዊ ምርጫ› በሞራል መሰረት ላይ የቆመ ልእልናን ለመጨበጥ ብትፍጨረጨር ይገርማልን? ወያኔ በ97 ምርጫ ለመሳተፍና ሌሎቸም ተቀናቃኞች በተወሰነ ነጻነትም ቢሆን እንዲንቀሳቀሱ የፈቀደበት ዋናው ምክንያት ይህ ብቻ ነበር።

***<u>የተቃዋሚ ድርጅቶች እይታ</u>***

የወያኔ ተቃዋሚ ድርጅቶች ቁጥር ብዙ ከመሆኑም በላይ፤ በአመለካከትም በጣም የተለያዩ አካላትን ይጠቀልላል። ስለዚህ፤ የተቃዋሚ ድርጅቶች እይታ ብሎ እኒህን ሁሉ የሚወክል አንድ ወጥ እይታ ማቅረብ አስቸጋሪ ይሆናል። በዚህ ንኡስ ርእስ ስር የተቃዋሚ ድርጅቶች እይታ በምንልበት ወቅት ልናቀርብ የምንሞክረው፤ በምርጫ 97 ሂደት ውስጥ ተጽእኖ ሊያሳርፉ ከቻሉት ውስጥ አብዛኞችን ጠቅልሎ የሚገኘውን በኢዴሀህ( የኢትዮጵያ ዴሞክራሲ ሃይሎች ህብረት) እና በቅንጅት ውስጥ የተካተቱትን እይታዎች ብቻ ነው።

---

[4] አስተማማኝነቱ የሚመጣው፤ እኒህ ተለጣፊዎች በየአካባቢያቸው የሚካሄደውን ምርጫ ለመቆጣጠር የሚያስችል ዝግጅት ስላላቸው ነው።

[5] በነገራችን ላይ፤ የኢህአዴጉ ደናቁርት በዚህ ወቅት፤ መለስ ትኩረቱ ሁሉ ወደ አለም አቀፋዊው ሁኔታ በመዞሩ ሀገሪቱ ተጎዳች! ይሉ ነበር፤ ይባላል።

እነዚህ ድርጅቶች የተለወጠውን የምእራባውያን እይታ ቀድመው ተደርገው ከነበሩ የኢትዮጵያ ምርጫ ተለምዶዎች ጋር በማገናዘብ፤ በ97 ምርጫ ወቅት 1) ድርጅቶቹን በአነስተኛ ፕሮግራም ዙሪያ ማስተባበር፤ 2) በውድድር ጣቢያዎች የተቃዋሚ ደጋፊዎች ድምጽ ተከፍሎ፣ በክፍፍሉም ወያኔ እንዳይጠቅም ተቃዋሚው በሚወዳደርባቸው ቦታዎች ሁሉ አንድ ተወካይ ብቻ እንዲያቀርብ፤ 3) በውጭ ከሚገኙ አካላት ለተቃዋሚዎች የሚቀርቡ ድጋፎችን በጋራ ዘመቻ ማሰባሰብ እንደሚያስፈልግ ተገንዝበዋል፡፡ ይህንንም እቅድ ከግቡ ለማድረስ እኒህን አካላት ያሰባሰበ ህብረት ከምርጫው ወቅት አንድ ሁለት አመታት ቀደም ብሎ ተፈጥሮ መንቀሳቀስ የጀመረበት ሁኔታም ነበር፡፡

ይህ አካሄድ ግን ብዙም ሳይገፋ፤ በአንድ አመት ጊዜ ውስጥ የተወሰኑ ድርጅቶች በተፈጠረው ህብረት ላይ ከአግባቡ በላይ የሆነ ተጽእኖ ለመሳደር በመሞከራቸው እና እንዲሁም በአንዳንድ ድርጅቶች መሪዎች የገጸ ባህርይ አለመጣጣም ምክንያት ወዲያውኑ ተቋረጠ፡፡ ከህብረቱ ራሳቸውን ያገለሉት ድርጅቶችም መኢአድ (መላው ኢትዮጵያ አንድነት ድርጅት) እና ኢዴፓ (ኢትዮጵያ ዴሞክራቲክ ፓርቲ) በመባል የሚታወቁት በሀገር ውስጥ ከሌሎቹ ድርጅቶች ሁሉ የበለጠ ደጋፊ ሊኖራቸው እንደሚችል የሚገመቱት ነበሩ፡፡ የሚያሳዝነው ግን፤ ሁለቱም በጋራ አንድ ላይ ሁነው ለመቆም ያልቻሉ ስለነበር፤ በዚያን ወቅት ተቃዋሚው ወገን ሶስት ቦታ ተከፍሎ ወደ ምርጫው እንደሚገባ ሁኖ የታየ ነበር፡፡

በዚህ ወቅት ነበር፤ የሁኔታውን አሳዛኝነት የተረዱ ወገኖች ራሳቸውን ቀስተ ደመና በሚል ድርጅት ዙሪያ አሰባስበው ከእነዚህ ሁለት ድርጅቶች ጋር ለምርጫው ሲባል ህብረትን ለመፍጠር የተንቀሳቀሱት፡፡ ቀስተ ደመና ከተፈጠረ በኋላ የተቃዋሚ ድርጅቶች አሰላለፍ የፖለቲካ ርእዮትን ሁለት ንኡሳን ህብረቶች ዙሪያ ተሰባስቦ የቀጠለ ነበር፡፡ በአንድ በኩል ቅንጅት ኢዴሊን (የኢትዮጵያ ዴሞክራቲክ ሊግ ) ጨምሮ ሀገር-አቀፍ የሆኑ ድርጅቶችን ሲይዝ፤ በሌላ በኩል ደግሞ አካባቢያዊና ክልላዊ የሆኑ ድርጅቶችን የያዘው ህብረት ሁኖ ወጣ፡፡

ህብረቱ የአካባቢያዊ ድርጅቶች ስብስብ መሆኑ፤ ከምርጫው የሚጠብቀውን ውጤት ግምት በመጠኑ የሚጠቁም ነበር፡፡ በዚህ ጽሑፍ መጨረሻ አካባቢ እንደምንመለከተውም፤ ይህ የህብረቱ ክልላዊ ቁመና በመጨረሻው ሰአት ወደ ፓርላማ ለመግባቱ ውሳኔ ተጽእኖ ነበረው፡፡ ከዚህ በመለስ ግን፤ የህብረቱ አባላት ሁነው በሀገር ውስጥ ይወዳደሩ የነበሩት ፓርቲዎች ከነበራቸው የድጋፍ ስፋት መጠን በመነሳት ስለምርጫው ውጤት የነበራቸው ግምት፤ የተወሰኑ መቀመጫዎችን በማግኘት ከማጠናቀቅ ያለፈ አልነበረም፡፡ እንደ እውነቱ ከሆነ፤ ይህ እይታ ከምርጫው ወቅት ጥቂት ወራት ቀደም ብሎ በነበረው ጊዜ ቅንጅትም የሚጋራው ነበር፡፡ ይህ ውሱን የሆነ የቅንጅት እይታ የመነጨው የድጋፍ መሰረት የለኝም ከሚል ስጋት አልነበረም፡፡ ይህንን ድጋፍ ለምርጫው ለማንቀሳቀስ የሚያስችል ድርጅታዊ ዝግጅት አለመደረጉን ከመገንዘብ ነበር፡፡ ዙሮ ዙሮ ከምርጫው በፊት የነበሩትን ጥቂት ወራት ስንመለከት፤ በሁሉም ተቃዋሚ ወገን ዘንድ ይህንን ምርጫ በአብላጫ ድምጽ በማሸነፍ እናጠናቅቃለን የሚል ግምት እንዳልነበር መናገር ይቻላል፡፡ "ማሸነፍ እንችላላን ብለን ከልብ አምነን ነበር" የሚሉ ቢኖሩም ወያኔ ከሽንፈቱ ተነስቶ ለሚፈጥረው ችግር አስቀድመው መፍትሄ አለማዘጋጀታቸው አባባላቸው ከልብ የተደረገ መሆኑን እንድንጠረጥር አድርጎናል፡፡

ይህ ሁኔታ መለወጥ የጀመረው፤ ተቃዋሚዎች ከወያኔ ባለስልጣናት ጋር በቴሌቪዥን ያደርጉት የነበረው ክርክር የህዝብን ቀልብ እየሳበ ሂዶ ብዛት ያለውን የህዝብ ቁጥር ማንቀሳቀስ ሲጀምር ነበር፡፡ ይህ ሁኔታ የፈጠረው የህዝብ ተነሳሽነት በአዲስ አበባው የሚያዝያ 30 ትእይንተ ህዝብ ሲጠናቀቅ፤ ተቃዋሚዎች በፓርላማ አብላጫ ድምጽ ባያገኙ እንኳን የተወሰኑ አካባቢያዊ መንግስታትን መቆጣጠር የሚችሉበት እድል እየታየ መጣ፡፡ ተቃዋሚዎች በዚህ ወቅት የታየውን የህዝብ ተነሳሽነት ከምእራባውያን መንግስታት እይታ ጋር አዳምረው በመመልከት የምርጫው አካሄድ ግልጽ እና ፍትሀዊ እንዲሆን ጠብቀዋል[6]፡፡ ሆኖም ግን፤ በራሳቸው ወገን የነበረውን ዝርክርክነት ታሳቢ በማድረግ ምርጫውን በአሸናፊነት እንወጣለን የሚል ልባዊ

---

[6] የተቃዋሚው ድጋፍ እየበረታ በሚሄድበት ወቅት፤ የወያኔ መንግስት ምንም ከማድረግ ታቅቦ መቀመጡ ሁሉንም ወገን በወቅቱ ያስገረመ ነበር፡፡ ይህ ሁኔታ በተቃዋሚዎች ዘንድ የተነበበውም፤ ወያኔ ምእራባውያን ምንም አይነት እመቃ እና አፈናን እንደማይፈቅዱ ከመረዳቱ እንደሆነ ተደርጎ ነበር፡፡ ወደኋላ ዞር ብለን ስንመለከተው ግን፤ ይህ ሁኔታ የተከተለው ወያኔ ‹እሸነፋለሁ› ብሎ ካለማሰቡ ብቻ ነው፡፡ የመለስ ዜናዊ የቁማርተኛነት ደመ-ነፍስ ታላቅ አስተዋጽኦ የነበረው ይመስላል፡፡

እምነት እንደነበር የሚያሳይ መረጃ የለም፡፡ ለፕሮፓጋንዳ በአፋቸው ከተናገሩት ያለፈ በተጨባች ዝግጅት የተደገፈ እምነት ማለታችን ነው፡፡

## *የአብዛኛው ህዝብ እይታ*

በምርጫው ማስገምገም ጅማሮ የነበረው የአብዛኛው ህዝብ እይታ የጨለምተኛነት ነበር፡፡ ከወያኔ ክፋት እና ጭካኔ ጋር ለ16 አመታት አብሮ የኖረው ህዝብ፤ ወያኔ በሰላም ስልጣኑን ይለቃል የሚለው ጉዳይ፤ ሲገባው አልቻለም ነበር፡፡ በቅንጅት እና በህብረቱ ውስጥ የተሰባሰቡት የሀገሪቱ ታላላቅ ምሁራን፤ በቴሌቪዥን እየቀረቡ ከወያኔ ካድሬዎች ጋር ያደረጓቸው ክርክሮች እና ህዝቡ የምርጫ ካርዱን እንዲጠቀምበት ያደረጉት ቅስቀሳ የህዝቡን እይታ እየለወጠው ሄደ፡፡ ይህ የተለወጠ እይታ የተከተለው ህዝቡ ስለሁኔታው መለወጥ ካደረገው ንባብ ሳይሆን፤ ለምሁራኑ ከሰጠው አመኔታ ነበር፡፡ እንደ እውነቱ ከሆነ፤ የተቃዋሚ ድርጅቶችን የድፍረት አነጋገሮች[7] ላስተዋለ፤ ከጀርባቸው የተማመኑበት ነገር ቢኖር ነው፤ የሚያሰኝም ነበር፡፡ በምርጫው የቅስቀሳ ወቅት ወያኔ በሰላም ከስልጣን እሺ ብሎ ስለመውረዱ በወሎ አርሶ አደሮች ለምሁራኑ ለቀረበላቸው ጥያቄ የሰጡት ምላሽ "እናንተ ምረጡንና እናሸንፍ፤ አልወርድም ቢል ጌቶቹ( አሜሪካኖች መሆናቸው ነው ) አይለቁትም" የሚል ነበር፡፡ የተወሰነው የህዝብ ክፍል ይህንን የተቃዋሚዎችን ስብከት ከተቀበለ በኋላ ግን፤ ማንም ሊቆጣጠረው የማይችል ዳይናሚክስ/እንቅስቃሴ ተጀመረ፡፡ ሲያመነታ ከነበረው ወገን መሀል ከፊሉ፤ የወያኔን መወገድ ለማጣደፍ ሲነሳ፤ የተወሰነው ደግሞ ወያኔ ሲነዛው ለነበረው የዘረኛነት ስብከት ሰለባ በመሆን ዘርን መሰረት ባደረገ እይታ ብቻ ከወያኔ ጎን ለመሰለፍ ወሰነ፡፡ ህዝቡ ያልተረዳው ጉዳይ ግን፤ ያ ሁሉ የተቃዋሚዎች የድፍረት ቃላት ጋጋታ ይጎርፍ የነበረው ከጥንካሬ ሳይሆን ድክመትን ለመሸፈን ከመፍጨርጨር መሆኑን ነበር፡፡ በሚገርም መንገድ ይህ የትርጉም ልዩነት፣ ህዝብ የተቃዋሚዎችን የድፍረት የቃላት ጋጋታ ከጥንካሬ እንጂ ድክመትን ለመሸፈን እንደመጣ አድርጎ አለማየቱ የምርጫ 97 ህዝባዊ እንቅስቃሴ መብራት እንዳይጠፋ ታላቅ አስዋጽኦ አድርጓል፡፡

እንግዲህ፤ ስለ ቅድመ-ምርጫ 97 የነበረው እይታ ሲጠቃለል፤ ከላይ የተጠቀሱት አራት የመድረኩ ተዋንያን ወይም አካላት ስለመጪው ታላቅ ታሪካዊ ሁነት የየራሳቸውን እይታ ይዘው የቀረቡ ሁነው እናገኛቸዋለን፡፡ በመሆኑም፤ ከምርጫ 97 ስለሚከተለው ውጤት የነበረው ግምት የተለያየ ሁኖ ይገኛል፡፡ ከህዝቡ በስተቀር የቀሪዎቹ ሶስቱ እይታ ተመሳሳይነት የነበረው ሁኖም ይገኛል፡፡ ህዝቡ ግን የመብት ባለቤትነቱ እውን እንደሚሆን አንድ ጊዜ ከተነገረው በኋላ በዚያው እይታ ላይ ጸንቶ መብቱን በእጅ ለማድረግ ማናቸውንም መስዋእትነት ለመክፈል ተዘጋጀ፡፡ ይህም ከምርጫ 97 ውጤት መታወቅ የቀጠለውን ፍጥጫ እና ግጭት አስከተለ፡፡

## 2- ከምርጫ 97 ውጤት መነገር መጀመር ቀጥሎ የመጣው ፍጥጫ እና የእንቅስቃሴው ድክመቶች

የውጭ ታዛቢዎች በብዛት በነበሩባት አዲስ አበባ፤ የምርጫው ውጤት ለህዝብ ይፋ ሲደረግ በእውነትም የወያኔ ፍጻሜ የቀረበ መስሎ ታየ፡፡ ሁሉም በዚህ ያልታሰበ ውጤት ተደናብሮ እያለ፤ ወያኔ ሁኔታውን ለመቆጣጠር የሚያስችል ተነሳሽነትን ወሰደ፡፡ በግንቦት  አዲስ አበባ በጊዜያዊ አስቸኳይ ሁኔታ አዋጅ ስር እንድትሆን ከመወሰኑም በላይ፤ የፌዴራል ፖሊስ አዛዥነትን መለስ ዜናዊ ተረከበ፡፡ የምርጫ ቆጠራው ባልተጠናቀቀባቸው አካባቢዎች ሁሉ የነበረው ቆጠራ ተቋረጠ፤ ታዛቢዎችም ከምርጫ ሳጥኖች አካባቢ ተባረሩ፡፡ መለስ ዜናዊ በተለያዩ መስመሮቹ የውጭ ሀገር መንግስታትን በሀገሪቱ አንዣብቦ የሚገኘውን አደጋ ለመወጣት እርሱ የወሰደው ርምጃን አስፈላጊነት ለማሳመን  እንቅስቃሴ አደረገ፡፡

ይህ ፈጣን የውሳኔ ርምጃ ሁሉንም አካል አደናበረ፡፡ ምእራባውያን መንግስታት የሁኔታዎች መለወጥ ያሳሰቧቸው መሆኑን ከመግለጽ ውጭ፤ ሁኔታዎች ወዴት እንደሚሄዱ ከመታዘብ ያለፈ ፍላጎት የነበራቸው አይመስልም፡፡ ህዝቡም ቀደም ብለው ካነሳሱት እና ካደፋፈሩት ተቃዋሚ ድርጅቶች የተግባር አቅጣጫ እንደሚመጣ በመጠበቅ ላይ ቆመ፡፡ ተቃዋሚ ድርጅቶቹ ግን ፈጽሞ ያልተዘጋጁበት ሁኔታ ሲከሰት፤ ከወያኔ

[7] በታሪካዊ ምጸት ከዚህ አንጻር ሲረሳ የማይችለው፤ የልደቱ አያሌው ድንፋታዎች ነበሩ፡፡

አካሄድ ጋር የሚመጥን የእይታ ሽግሽግ ማድረግ አልቻሉም። በስእላዊ አነጋገር ሲገለጽ ተቃወሚዎች የአዳኟን ጥይት አይኗን ጨፍና የምትጠብቅ ሚዳቋን የመሰለ ሁኔታ የሚያንጸባርቁ ነበሩ፤ ማለት ይቻላል።

ለዚህ የተቃዋሚዎች የመደናበር ሁኔታ መከተል፤ የሚቀጥሉት ሶስት ውስጣዊ ምክንያቶች በዋነኛነት ሊጠቀሱ የሚገባቸው ናቸው።

1. **ድርጅታዊ ጥንካሬ፤-** ከላይ እንደተገለጠው ተቃዋሚ ድርጅቶቹ በህብረት መሰባሰብ የጀመሩት ወደ ምርጫ ሊገቡ ጥቂት ጊዜ ሲቀራቸው ብቻ ነበር። በዚህም ምክንያት ድርጅታዊ መዋቅሩ ከስር ባለው የህዝብ መሰረት ዘንድ ገና ስር ያልሰደደ ብቻ ሳይሆን፤ ጥቂቱም ጅማሮ ለወያኔ ስለላ የተመቻቸ ሁኖ እንዲቀመጥ ያደረገ ነበር። ይህም፤ ተለዋዋጭ ሁኔታዎች በሚፈጠሩበት ወቅት አስፈላጊ የሆነውን የአመለካከት ሽግሽግን እና አንድ ወጥ የሆነን ስሉጥ ድርጅታዊ ምላሽን ከተቃዋሚዎች አቅም ውጭ እንዳደረገው ታይቷል።
2. **ርእዮት ቀመስ ትብተባ፤-** የተቃዋሚዎች ድርጅታዊ ቁመና ከላይ የተገለጸውን መስሎ ሳለ፤ ‹በእንቅርት ላይ ጆሮ ደግፍ› እንዲሉ ደግሞ፤ የርሱም አካሄድ ሰላማዊ ትግል በተባለው ርእዮት ቀመስ በሆነ ትብትብ የታነቀ ነበር። ይህ ጉዳይ ከሌሎች ሁሉ በላቀ ደረጃ እንቅስቃሴውን እስካሁን ድረስ አንቆት የሚገኝ በመሆኑ በጥቂቱ ሰፋ አድርጎ መመልከት ተገቢ ይሆናል።

   እንደሚታወቀው ሁሉ፤ በምርጫው ለመሳተፍ አንዱ ቅድመ ሁኔታ የአመጽ ትግልን መንቀፍ ስለነበር፤ በምርጫው ለመወዳደር የተሰለፉ ድርጅቶች ሁሉ የሰላማዊ የትግል ስልት ደጋፊዎች ሁነው መቅረባቸው ግዴታ ነበር። ነገር ግን፤ ለዚህ አቋም የነበረው ጽናት በሁለቱ ህብረቶች መሀል የተለያየ ነበር። በኢዴሀህ በኩል የነበረው እምነት በጥቅሉ ሲታይ ከተግባራዊነት የመነጨ ነው። ይህንን የምንለው በምርጫው ውስጥ የተሳተፉት ኦብኮ እና ደህዴን አመጽን ይደግፋሉ ለማለት ሳይሆን፤ በአብዛኛው በውጭ ሀገሮች ውስጥ የሚንቀሳቀሱት የህብረቱ አባላት የመሳሪያን ትግል አስፈላጊነት የማይክዱ መሆናቸውን ከመገንዘብ ነው።

   በቅንጅት አካባቢ የነበረው ሁኔታ ግን ከተግባራዊነት አልፎ፤ ሰላማዊ ትግልን ከዲሞክራሲ ስርአት ምስረታ ጋር የሚያያይዝ ርእዮታዊ ትንተናን ያቀፈ ነበር። እንደ ቅንጅት እይታ ሰላማዊ ያልሆነ ትግል ግልጽነት የሌላቸው አካሄዶችን ስለሚያስከትል ለጸረ-ዲሞክራሲያዊ አሰራሮች በርን ይከፍታል። ከዚህም በመከተል፤ የመጨረሻ ውጤቱ ከታለመው ግብ ርቆ ያለ አምባገነናዊ መድረሻ ላይ የመጠቃለል አቅሙ ትልቅ ይሆናል። ከዚህ በተጨማሪ ደግሞ፤ ሀ) ጦርነት በሀገሪቱ ላይ እስካሁን ያደረሰውን አደጋ፤ ለ) በሀገራችን ለዘመናት የሚሽከረከረውን የጦርነት አዙሪት ላንዴና ለመጨረሻ ጊዜ መሰበር እንዳለበት፤ ሐ) ከወያኔ አገዛዝ ተከትሎ በሀገራችን የተፈጠረው ዘርን መሰረት ያደረገ ክፍፍል ባለበት ሁኔታ የአመጽ እሳትን መጫር መጨረሻ ወደሌለው የርስ በርስ ጦርነት መሸጋገሪያ መሆኑን በማገናዘብ፤ የአመጽ ትግል ሊታሰብ እንደማይችል ታምኗል።

   ይህ ከላይ የተቀመጠው የቅንጅት እይታ በቁሙ ሲታይ ምንም አሌ የሚባል ባይሆንም፤ ትግሉ የተለየ ሁኔታ ሲገጥመው እንዴት እንደሚቀጥል የሚያመለክት ፍንጭ የሌለው መሆኑ ግን ትልቅ ስህተት ነበር። ሌላው ቀርቶ፤ ስለ ሰላማዊ የትግል ስልቶች በጸጋ የተባለውን ሁሉ ተቀብሎ፤ ይህ ትግል ህጋዊ መድረኩ ሲዘጋበት በሚስጥራዊ አደረጃጀት ሊመራ የሚችልበትን መንገድ ለመቃኘት አለመሞከሩ ይገርማል። እንደ እውነቱ ከሆነ፤ ለእይታው ከተሰጠ የአመኔታ ጽናት ይልቅ፤ ቀደም ተብሎ ቅንጅት ወደ ምርጫው ሲገባ ከነበረው የተከፈለ ልብ ሁኔታ ራሱን ለማላቀቅ ያልቻለ መሆኑን የሚያሳይ ነው። እዚህ ላይ አንባቢ ልብ እንዲል የምንፈልገው አስተያየታችን የቅንጅትን ለጋነት በወቅቱ የገጠሙትን ፈተናዎች፣ መሪዎቹ እርስ በርስ በሚገባ ያለተዋወቁበት ሁኔታ የሚፈጥረውን እንቅፋትነትና ይህም ሁሉ ሆኖ ቅንጅትን ለምርጫ ለማብቃት አላማውን ለመግለጽ ሌሎችንም አስቸጋሪ ስራዎች ለመስራት በመሪዎቹ የተከፈለውን መስዋእትነትና የመሪዎቹን ድካም የተገኘውን ድል አሳንሰን በማየት የሚቀርብ አይደለም። የዴሞክራሲ ትግሉ ትልቅ ችግር ውስጥ ገብቷል ብለን በምንጨነቅበት በእዚህ ታሪካዊ ወቅት ለሁሉም የሚገባውን ምስጋናና ክብር

በመዘርዘር ብእራችን የምናደክምበት ሰአት አይደለም ብለን ስለምናምን ብቻ ነው ይህ ጉዳይ ያልተነሳው። ከእዚህ በተጨማሪ ግን ቅንጅት በምርጫው ወቅትና በኋላ ካሳያቸው ጥንካሬዎቹ ጋር ተያይዘው የሚገኙና መተቸት ያለባቸው ድክመቶች ያሉት ድረጅት ነው ብለን ግን እናምናለን።

3. **ስለ ምእራባውያን መንግስታት የነበረ አመለካከት፤-** ቅንጅት ምእራባውያን በአለም አቀፍ ፖለቲካ ውስጥ ከመርህ ተነስተው ለዴሞክራሲ የሚሰጡትን ስፍራ እጅግ ከሚገባው በላይ አጋኖ አይቶታል። ምእራባውያን በተለይ አሜሪካ በዚህ ጥያቄ ላይ ሁለት አይነት መስፈርት ይዛ የምትጓዝ መሆንዋ ደጋግሞ የታየ ነው። ዴሞክራሲ የሚታያቸው የማይወዷቸውን አምባገነኖች ለመገሰጽ ወይም ለማስፈራራት ሲፈልጉ፤ አለበለዚያ ግን እነ ሞቡቱን የመሰሉ ነፍሰ በላዎችን ሁሉ የነጻው አለም ወዳጆች እያሉ ሲያሞካሹ መኖራቸው የቅርብ ጊዜ ትዝታ ነው። የኢትዮጵያ ሁኔታ ያስመሰከረው ጉዳይ፤ ቀደም ብሎ የተገለጸው የአሜሪካኖች አለማቀፋዊ እይታ ለውጥ ሙሉ ጉዞውን እንዳልፈጸመ ነው። ከሶቪዬት ህብረት መውደቅ በፊት አሜሪካኖች እናምንበታለን ያሉት ፍልስፍና በጸረ-ኮሙኒዝም ትግል መተብተቡን በሚያንጸባርቅ ደረጃ፤ ያሁኑም የቡሽ ርእዮት ጸረ-ሽብር በሚል ምትሀታዊ ቅዠት ተተብትቦ ይገኛል። ከሚታዩት አመልካቾች መገምገም የሚቻለው ይህ የተምታታ ሁኔታ በቅርቡ መጥራቱን ሳይሆን፤ የአሜሪካ የውጭ ጉዳይ ፖሊሲ እንደወትሮው በቅራኔ ተወጥሮ ግልጽ ባልሆነ "የአሜሪካን ብሄራዊ ጥቅም" ማስጠበቅ በሚል መርሆ ዙሪያ ብቻ የሚሽከረከር መሆኑን ነው።

   ከዚህ በተጨማሪ ተቃዋሚው ወገን መረዳት የሚኖርበት ጉዳይ ደግሞ፤ መለስ ዜናዊ አሜሪካኖች እና እንግሊዞች አሳድገው ለስልጣን ያበቁት መሆኑን ነው። መለስ ዜናዊ ራሱን የሚያውቀውን ያህል አሜሪካኖችም የመለስ መንግስት ካለእነርሱ ድጋፍ እንደማይቆም ስለሚረዱ የታዘዘውን የሚፈጽም ተላላኪያቸው መሆኑን ያውቁታል። ታዲያ እንዲህ አይነቱ ተላላኪ እንደ አማራጭ ሁኖ ባለበት ሁኔታ ውስጥ፤ ስለሀገር ክብር የሚያወሩ አካላትን አሜሪካኖች ካለአንዳች አስገዳጅ ሁኔታ እንዴት ሊመርጡ ይችላሉ ብሎ ማሰብ ይቻላል?

   እንደእውነቱ ከሆነ ደግሞ፤ የመለስ ዜናዊን ብልጣ ብልጥነት በዚህ ላይ ደርቦ መመልከትም ተገቢ ነው። መለስ ዜናዊ በሩቁ ማሰብ የማይችል የእለቱን ብቻ ለመወጣት ብቻ ሲያሰላ የሚውል እና የሚያድር ትልቅ ታክቲሺያን ነው። በመሆኑም፤ በአሜሪካኖቹ አይን ከተቀናቃኞቹ ጋር ሲተያይ ለርሱ የሚኖረውን ቅድሚያ በአግባቡ ተረድቶ የተጠቀመበትም ነው። መለስ ዜናዊ ኢዲ አሚን ያላነሰ ጨፍጫፊ፤ ከሞቡቱ ያላነሰ ዘራፊ ቢሆንም ስለዴሞክራሲ እና የመልካም አስተዳደር ስርአት ምስረታ የሚታገል ሁኖ ለመታየት ሁልጊዜም እንደጣረ ነው። በምእራብ መንግስታት የውጭ ፖሊሲ ሃላፊዎች ዘንድ ይህ አይነቱ ግንዛቤ እንዲሰርጽ ደግሞ፤ በመንግስት ስልጣን ባለቤትነቱ በእጁ ያስገባውን ሃብት ለድለላ እና ለሽንገላ ስራ እንዳሻው ይጠቀምበታል። ገንዘብ ለፈለገው ገንዘብ፤ የወሲብ ዛር ነፍሱን ለሚያሽከረክረው የፈለገውን፤ ከእግዚያብሄር በታች ያለ እርስዎ መባል ለሚፈልግ ከንቱና የረቀቀ ፉገራ፤ እንደ የሀገሩ መሳፍንት መኖር ለሚፈልገው በጋሻ የሚቆጠሩ የኤምባሲ መኖሪያ ክልሎች እና እርሱን እንዳያጣ የሚያሳስቡ ማስፈራሪያዎች ይቀርባሉ። ከዚህ በተጨማሪ ደግሞ፤ በየሀገሩ የሚገኙ በውጭ ጉዳይ ፖሊሲ ላይ ተጽእኖ ሊያሳድሩ የሚችሉ ጋዜጠኞች፤ ታዋቂ ሰዎች፤ ፖለቲከኞችን ወዘተ… በወዳጆቻቸው እና በሎቢ ኩባንያዎች በኩልም ይቀረባሉ። ይህ ሁሉ ጥረት ሲጠቃለልም፤ የተቃዋሚ ድርጅቶች ድምጽ ባዶ ሜዳ ላይ እንዲቀር የሚያደርጉ ሁኔታዎች ለመፍጠር ተሞክሯል።[8]

[8] ሌላው ቢቀር፤ የካርተር ማእከል በካርተር መሪነት ምርጫውን አስመልክቶ የወሰደውን ቀፋፊ አቋም በሌላ መንገድ መረዳት አይቻልም። ካርተር በቢቢሲ ቴሌቪዝን ላይ ‹ቶኒ ብሌር ቡሽን ጠንክሮ መከራከር እንጂ እንደታዘዘው መስራቱ ለሁሉም ወገን ጥሩ አልነበረም› እያለ ሲከራከር ለሰማ፤ ከላይ የተጠቀሰውን የመለስ ዜናዊ ሎቢይስቶች ስራ ላላስተዋለ፤ ይህ ሰው በኢትዮጵያው የ97 ምርጫ ላይ የወሰደውን የተወላገደ አቋም መረዳት ይስቸግረዋል። ካርተር አዲስ አበባ እንደደረሰ ተቃዋሚዎች የሚመጣውን ሽንፈት በጸጋ እንዲቀበሉ ከማሳሰብ ተነስቶ፤ በምርጫ መጭበርበሩ ዙሪያ የተነሳው ውዝግብ የኢትዮጵያ ዳኞች ራሳቸው እየመሰከሩበት በነበረው በመለስ ዜናዊ ካድሬዎች በሚዘወረው መሳቂያ ፍርድ ቤት እንዲታይ የሚወተውት ነበር።

ስለዚህ አሜሪካኖች በኢትዮጵያ የሚደረገው የዴሞክራሲ ትግል በፍትሀዊነት የሚጠናቀቅበት መንገድ እንዲደግፉ የማድረጉ ሁኔታ፣ ዝም ብሎ በራሱ የሚመጣ ሳይሆን ብዙ ትግልን የሚጠይቅ ነው፡፡ ይህ ፍትሀዊ አማራጭ ለአሜሪካኖቹ እንዲታያቸው ደግሞ፣ ከሚከተሉት ውስጥ አንዱ ወይም ከዚያ ቁጥር በላይ ያሉ ጉዳዮች መከናወን ይኖርባቸዋል፣ ሀ) ሁኔታው ፍትሀዊ በሆነ መንገድ ካልተፈታ የሚከተለው ጉዳይ የአሜሪካኖችን ጂኦ-ፖለቲካዊ እና ስትራቴጂያዊ ጥቅሞች እንደሚያናጋ በተጨባጭ ማሳየት፣ ለ) የሚደግፉት መንግስት ቁመና አሳፋሪ መሆኑን ለሀገራቸው ነዋሪዎች እና ቀናነት ላላቸው የተለያዩ ተቋማት ማሳየት፣ ሐ) በኤምባሲዎቻቸው እና የተለያዩ ሌሎች መንግስታዊ ተቋማት ውስጥ ተሰግስገው በተለያዩ ጥቅማ ጥቅሞች እየተገዙ የመንግስታቸውን አቋም በመቅረጽ ረገድ ተጽእኖ ያላቸውን አካላት ማጋለጥ፡፡

ተቃዋሚዎች ምእራባውያን ለዴሞክራሲ ያላቸውን እምነት፣ ከመለስ ዜናዊ እንቅስቃሴ እና ከአሜሪካኖቹ የዘወትር ባህርይ ከሆነው በውጭ ጉዳይ ፖሊሲያቸው ውስጥ ከሚከተሉት የሁለት አይነት መስፈርት እውነታ ጋር ሳያገናዝቡ መቅረታቸው የእንቅስቃሴው ትልቁ ስህተት ነበር ማለት ይቻላል፡፡ ምክንያቱም፣ ይህ የአመለካከት ስህተት ድርጅታዊ አቅምን ለማጠናከር በትግሉ ላይ አደጋ ቢያንዣብብ አደጋውን ለመከላከል የሚያስችል የሃሰብና የድርጊት ዝግጁነት እንዳይኖራቸው ያደረገ ስለነበር ነው፡፡

እኒህ ከላይ የተዘረዘሩት ሶስት መነሻ ድክመቶች በአንድ ላይ ተደምረው ሲታዩ ከምርጫ 97 በመቀጠል የተከተሉትን ሁኔታዎች ተቃዋሚው በአግባቡ ያላሰበባቸው መሆኑን ያረጋግጣሉ፡፡ በቀን አንድ መለስ ዜናዊ የፖሊስ ስልጣንን ሲወስድ እና አስቸኳይ አዋጅ አዲስ አበባ ላይ ሲያውጅ፣ ተቃዋሚዎች ያደረጉት ነገር ለውጭ ኤምባሲዎች እና የምርጫ ታዛቢዎች ‹አቤት› ማለትን ብቻ ነበር፡፡ የዚያ አዋጅ አስፈላጊነት፣ መለስ ዜናዊ እንዳለው፣ መንግስት ውስጥ ያሉ አካላት በአዲስ አበባው ምርጫ ውጤት ተበሳጭተው የእልቂት እርምጃ እንዳይወስዱ ለመከላከል ሁኖ ቢሆን እንኳን፣ ለውጭ ኤምባሲዎች ‹አቤት› ከማለት የተሻሉ ብዙ እርምጃዎች ነበሩ፡፡ ቢያንስ እንዲያ ያለ አደጋ መኖሩ ሲታመን፣ ይህንን አደጋ በአስተማማኝ መንገድ መቆጣጠር የሚቻልበት መንገድ ታሳቢ መሆን ነበረበት፡፡ የሚመረጠው ደግሞ፣ የመለስ ዜናዊን ማንነት የሚስት ብዙ ሰው ስለማይኖር ያለውን አደጋ በታሳቢነት ይዞ፣ ቅጥፈቱን በማገናዘብ ለወደፊት ሊያደርግ ስለአሰባቸው ሁኔታዎች መላምቶችን መደርደር እና ከእነርሱም አንጻር ለእያንዳንዳቸው ተገቢ የሆኑ እርምጃችን አስቀድሞ መቀየስ መሆን ነበረበት፡፡

ለውጭ መንግስታት ይቀርብ የነበረው አቤቱታ፣ ሁኔታውን በዚህ አንጻር በመመልከት የተደረሰበት የትግል ስልት ነበር፣ ሊባል ይሞከር ይሆናል፡፡ እንደ መጀመሪያ የተወሰደ ትክክለኛ እርምጃ ተደርጎ ቢወሰድ እንኳን፣ ይህ አካሄድ ለውጥ አለማምጣቱ በጥቂት ሳምንታት ውስጥ እንደታወቀ፣ የራስን አቋም መመርመር እና ስለ ፈረንጆች ሚና የተወሰደውን ግምገማ እንደገና መመልከት ተገቢ ነበር፡፡

ተቃዋሚዎቹ እንዲህ አይነት ግምገማ ቢያካሂዱ ኑሮ፣ ሀ) የመለስ ዜናዊ አካሄድ ስልጣንን በማንኛውም ዘዴ ቢሆን ጨብጦ ለመቆየት መወሰኑን፣ ለ) የፈረንጆቹ አቋም አስተማማኝ አለመሆኑን፣ ሐ) የምርጫውን ውጤት ለማስከበር ዋናው መተማመኛ ከህዝብ ጋር በተራው ሰው ደረጃ በየአካባቢው የሚፈጠር መተሳሰር መሆኑን መገንዘብ ይቻል ነበር፡፡ ይህ አይነት አካሄድ በድርጅቶቹ ዘንድ አመኔታ የተሰጠው መሆኑ በህዝብ ዘንድ ቢስተዋል ደግሞ፣ ህዝብ ለተቀነባበረ ህዝባዊ ትግል በየራሱ ተነሳሽነት ሊዘጋጅ የሚችልበት እድል ይፈጠር ነበር፡፡ በዚህ አይነት የሚነሳሳ ህዝባዊ እንቅስቃሴ ስፋትን ካገኘ ደግሞ፣ ወያኔ በወታደራዊ ሀይል እቆጣጠረዋለሁ ብሎ ከማሰብ ሊታቀብም ይችል ነበር፡፡ ይህ ባይሆን መጨረሻው የሚታወቅ ባይሆን እንኳን፣ በየቦታው ህዝብ በግብታዊነት እየተነሳ በተደራጀው የወያኔ ሀይል ከመደምሰስ ይልቅ ከተቃዋሚ ድርጅቶቹ ለተቀነባበረው መነሳሳት እንዲጠብቅ ሊመከር ይችል ነበር፡፡

በዚያ አስቸጋሪ ወቅት፣ ተቃዋሚዎች ምንም አይነት አመራር መስጠት ባለመቻላቸው ህዝብ በየራሱ ተነሳሽነት በየቦታው የወያኔን ወታደራዊ ሀይል ሊጋፈጠው ተነሳ፡፡ በዚህም ምክንያት በህዝብ ወገን ላይ ብዙ እልቂት ሊደርስ ችሏል፡፡ ይባስ ብሎ፣ ፍጥጫውን በተመለከተ አመራር መስጠት ባይችሉ እንኳን በንግግር

ደረጃ ተጠያቂነቱን ወደ ገዳዮቹ ወደ መንግስት ባለስልጣናት ማዞር ሲገባ፣ ሰላማዊ ሰልፈኞቹን ለሁኔታው ተጠያቂ አድርጎ ለማቅረብ የተሞከረው ሁኔታ ተቃዋሚዎቹ በዚያን ወቅት ለመሪነት የሚሆን ብቃት የመጨበጣቸውን ሁኔታ ጥያቄ ውስጥ ያከተተ ጉዳይ ነበር። በዚያ ወቅት የታየው ዝርክርክነት በምእራባውያን ዘንድ በሚገኘው ስር የሰደደ የዘረኝነት እይታ ጋር ተዳምሮ፣ ‹ሀበሻ ይችን ያህል ካገኘ ይበቃዋል› የሚል አይነት አመለካከት ፈጥሮ ቢሆን ሊገርመን አይገባም[9]።

ይህ የአመራር ዝርክርክነት ምእራባውያንን ቸል እንዲሉ ያደረገ ብቻ ሳይሆን፣ በወያኔ የእመቃ መዋቅር ውስጥ ለእንጀራ ሲሉ የተሰለፉ፣ ነገሮች ሊለወጡ የሚችሉ ሁነው ቢታዩ ግን ከህዝብ ጋር የሚቆሙ አካላትንም ጭምር እንዲያፈገፍጉና እንዲያስቡ ያደረገም ነበር። ምክንያቱም፣ እኒህ አካላት እጣቸውን ከህዝብ ጋር ለማድረግ የሚነሱት የወያኔ መውደቅ እውን ይሆናል ብለው ካሰቡ ብቻ ስለሚሆን ነው።

በወያኔ በኩል የነበረው አካሄድ በአንጻሩ፣ ግቡን ያወቀ እና ለዚያ ግብ የሚያስፈልገውን ዝግጅት በፕሮጀክት መልኩ ቀርጾ የሚንቀሳቀስ ነበር። ወያኔ በራሱ በኩል ያለውን ዝግጅት እስኪያጠናቅቅ ድረስ ተቃዋሚዎቹን ማዘናጋት፣ የህዝቡ የትግል ስሜት እንዲቀዘቅዝ በሆነ ባልሆነው ነገሮችን ማጓተት፣ በተቃዋሚዎች መሀል ልዩነቶች ሊፈጠሩ የሚችሉባቸውን መንገዶች ሁሉ ማፈላለግን እና ተቃዋሚዎች በውጭ መንግስታት አይን ውስጥ የማይረቡ ሁነው እንዲታዩ ማድረግን ዋና ዘዴው አድርጎ ተንቀሳቀሰ። በተቃዋሚው ወገን የነበረው ታክቲክ በህጻንነታችን ‹ማስቦካት› እንለው ከነበረው የዘለለ አልሆነም። ለመስከረም የተጠራውን ህዝባዊ ትእይንት ከመለስ ዜናዊ ጋር በሚደረግ ውይይት የስልጣን ሽግግርን ለመፈጸም ታስቦ መሰረዝ፣ እንደ ሰገሌ ጦርነት ለትውልድ ሲሳቀበት የሚኖር ጉዳይ ነው። የሰኔን እልቂት ለተመለከተ፣ መለስ ዜናዊ ለመደራደር ቢገደድ እንኳን ካለ ህዝብ ተጽእኖ በነጻ ፈቃደኛነት ይህንን እንደማያደርግ መረዳት ሊቸግር አይገባም ነበር።

ይህ በወጉ ያልተሰላ የትግል አካሄድ ከድርጅታዊ አቅም አለመጠናከር የመጣ ብቻ አይደለም። ለዴሞክራሲ ከተሰጠ ተንሳፋፊ ልሂቃዊ ግንዛቤ እና የፖለቲካውን መደብ ለዘመናት ተጠናውቶት ከኖረው ምሁራዊ ስንፍናም ጋር ይያያዛል። በአብዛኛው የተቃዋሚ ድርጅት መሪዎች አካባቢ የነበረው አካሄድ፣ በተቻለ መጠን የህዝብን ቁጣ እንደማስፈራሪያነት ተጠቅሞ ከወያኔ የሚገኙ ምርኮዎችን ተቀብሎ ወያኔ የፈቀደውን የፓርላማ መቀመጫ ይዞ መጠናቀቅ ነበር። ‹ፓርላማ ሳንገባ እንችላለን› የተባለው ማስፈራሪያም በውጭ መንግስታት ላይ የተነጣጠረ ብቻ ነበር። በአፋቸው ስለ ዴሞክራሲ እና ስለ ህዝብ ሉአላዊነት ብዙ ቢሉም፣ አባባሎቻቸው ከጥልቅ እምነት የሚመነጩ ለመሆናቸው ማስተማመኛ አልነበረም።

ተቃዋሚዎች ለህዝቡ የሰጡት ሚና ‹ተኛ!› ሲሉት የሚተኛ፣ ‹ተነስ!› ሲሉት የሚነሳ ወያኔን አስፈራርቶ የስልጣን መንጠቂያ መሳሪያ ከማድረግ ያለፈ አልነበረም። እነ ልደቱን የመሰሉት ግልገል ፋሺስቶች ደግሞ፣ አስገድለውት ሬሳውን የፓርላማ መግቢያ ሰበብ ለማድረግም ያሰሉ ሁነው ይታያሉ[10]። ለህዝቡ የነበረ አክብሮት ዝቅተኛነት እና ስለ ህዝቡ ጉዳት እና ስሜት ብዙ ዴንታ ያለመስጠት ሁኔታ በሌሎች መልኮችም የታየ ነው።

ከላይ የጠቀስነው የህዝቡን አመጽ ከወያኔ ጎን ቁሞ የመኮነን ጉዳይ እንደተጠበቀ ሁኖ፣ ከዚያ በመቀጠል በወጡ የተለያዩ ጽሁፎች፣ በተደረጉ ንግግሮች እና በተቀየሱ የተግባር እንቅስቃሴዎች ወስጥ የግድያው ወንጀል ጎልቶ የሚወጣበትን መንገድ ስለመፈለግ የተሰጠው ትኩረት አነስተኛነት አንድ ምስክር ነው። ፓርላማ ለመግባት በሚታሰብበት ወቅት መጀመሪያ የተሞከረው፣ የህዝብን እይታ ከማስተናገድ ለመከለል ሲባል ‹የታዋቂ ሰዎች ምክር› ተብሎ የተጠቀሰው ሁኔታም ሌላ ምሳሌ ነው። በድርጅቱ ይሁን መሪዎቹ በተያዩ ግዜዎች በጻፏቸው ጽሁፎች ውስጥ ስለ ግድያው የሚታይ የመቆጨት እና የመቆርቆር ስሜት መጥፋትም በጣም አስደንጋጭ ነው።

---

[9] በዚያው ሰሞን በማከታተል የታዩት ጥፋቶች፣ ልደቱ አያሌው በቢቢሲ ራዲዮ ላይ የሰኔውን ተቃውሞ ሰላማዊ ሰልፈኞች በእንግሊዝኛ ችግር ይሁን በውስጥ አርበኛነት ‹ረብሸኞች› (rioters) ብሎ መጥራቱ፣ በዚያው ሰሞን ቅንጅት ያወጣው ሙታንን የሚወቅስ አሳፋሪ መግለጫ ሁሉ ለምእራባውያን ቸልታ አስተዋጽኦ ሊኖረው ይችላል።

[10] እንደ እውነቱ ከሆነ፣ ቅንጂት እንዲህ አይነት ወሬ በሹክሹክታ ደረጃ እንኳን ሊወራ የቻለበት መድረክ ከነበረ፣ ከዚህ መለስ ያሉ ጸረ-ህዝብ አስተያየቶችን የሚጋሩ ብዙ አካላት ሊኖሩ ይችላሉ ብሎ መጠርጠር አጉራ ዘለልነት አይሆንም።

በርግጥ፤ ይህ አካሄድ ለሰላማዊ ትግል ከተሰጠ ልባዊ አመኔታ የመነጨ ነው ሲባል ይሰማል። በጥንቃቄ ጉዳዩን ለሚመረምር ግን፤ አንዳንድ የማይመቹ ሁኔታዎችን ያዘለ አካሄድ መሆኑ ይስተዋላል። እስከ ሰኔው ግድያ ድረስ ‹ሰላማዊ እና ህጋዊ የትግል ስልት› የተባለውን አካሄድ መከተል ምንም አወዛጋቢነት አልነበረውም። ከዚያ በኂላ በተለወጠው ሁኔታ ውስጥ ከዚህ አካሄድ ጋር ሙጭጭ ማለት ግን፤ ከየት እንደሚመጣ መናገር አስቸጋሪ ነው። በርግጥ ወያኔ ሳንጃውን ሰክቶ ሰው ለማረድ ሲክለፈለፍ እንዲህ አይነቱ አካሄድ ያዋጣል ተብሎ ነው? ወይስ አማራጩን ከመፍራት ነው ?

ሁለቱም ምክንያቶች አግባብነት የሌላቸው መንደርደሪያዎች ነበሩ። የመጀመሪያው በወቅቱ በተጨባጭ ከነበረው እውነታ ጋር ለመፋጠጥ ካለመፈለግ የተወሰደ ምክንያት በመሆኑ ቀቢጸ ተስፋ ብቻ ነበር። ከዚህ ካለፈ ደግሞ፤ ከመሪዎቹ የኑሮ ሁኔታ ጋር ወደ ተያያዘ ትንተና እንድንገባ የሚያደርግ ነው። አብዛኞቹ በሀገሪቱ መስፈርት ከከፍተኛው ሀብታም ምድብ የሚገቡ በመሆናቸው፤ ሰላማዊ ያልሆነ አካሄድ የኑሮ ደረጃቸውን ሊያወላልቀው የሚችልበት ሁኔታ አስቀድሞ የታያቸው ሳይሆን አይቀርም። ወያኔም ቢሆን የቅንጅት ከፍተኛ አመራር ደፍሮ የማያደርገው ነገር የለም የሚል ስሌት እነደነበረው ግልጽ ነው። ከምርቻው በፊትና በኂላ የሚያስተላልፋቸው መግለጫዎች እራሱን በመከራ የተፈተነ ባላንጣዎቹን ግን ደፍረው ምንም ማድረግ የማይችሉ ቅምጥሎች አድርጎ ነበር። ወያኔ ምንም አይነት የማርያም መንገድ ሳይከፍትላቸው ያቀደውም ይህንን አስልቶና እና እኒህ መሪዎች አጣብቂኝ ውስጥ ቢወድቁ በሚወስዷቸው ውሳኔዎች በህዝብ ሊተፉ ይችላሉ፤ የሚል ስሌትን ይዞ ነበር[11]።

ስለ ሰላመዊ ትግል የተባለው ሁሉ የአመጽን አማራጭ ከመፍራት የተወሰደ አቅጣጫ ነው፤ የሚለውም በአግባብ ባለው ትንተና የተደረሰበት መደምደሚያ ሳይሆን፤ ያሉበትን ሁኔታ ለመከላከል ሲል የቀረበ ድብስብስ ክርክር የሚመስል ነገር ነበረው[12]። ስለሰላማዊ ትግል ጸጋ የተባላው ሁሉ እውነት ቢሆንም፤ በዚያን ወቅት ሰላማዊ ትግል ማድረግ ይቻላል ወይ? ካልተቻለስ ምን ማድረግ ይገባል? የሚሉትን ጥያቄዎች ለማንሳት እንኳን የደፈረ አልተገኘም። እንዲያው በደፈናው ትግሉን በቁማር መልክ መያዝ ነበር የተመረጠው። ለሁላችንም አሁን ግልጥ ሁኖ እንደሚታየን፤ በዚያን ወቅት ተነስተው ምላሽ ሊሰጣቸው የሚገቡ ጉዳዮች በንሁልልነትና በቸልታ በመታለፋቸው ባለፉት ሁለት አመታት ውስጥ ትግሉ መላ አቅሙን አስባስቦ እንዳይሄድ አድርጓል።

እንግዲህ በ1998 መጀመሪያ አካባቢ የነበረው የተቃዋሚ ድርጅቶች ሁኔታ ከላይ በተገለጸው መልክ ተስፋ አስቆራጭ መስሎ ቢታይም፣ በአንድ በኩል ‹መብትህ ካልተከበረ እንሞትልሀለን!› ተብሎ ተቀስቅሶ የወጣው ህዝብ ስለመብቱ መከበር ያሳየው የትግል ጽናት በሌላ በኩል ደግሞ የተቃዋሚ ድርጅቶችን የአመራር ብቃት ማነስ እና የእምነት ጉድለትን አጋልጧል። በአዎንታዊ መልኩ ደግሞ፤ በዚህ እንቅስቃሴ ዘመን ውስጥ በቅንጅት የተወሰደውን የፓርላማ አለመግባትን፤ ብቸኛ ትክክለኛ አቋም እንዲያዝ በማድረግ የትግሉ ችቦ እንደተቀጣጠለ እንዲቀጥል እና ቅንጅትን ከታሪክ ትቢያነት እንዲድን አድርጓል።

**3-የግንቦት 97 ህዝባዊ እንቅስቃሴ ድሎች**

የግንቦት 97ቱ ህዝባዊ እንቅስቃሴ ከላይ በተገለጹት አይነት አስቸጋሪ ሁኔታዎች ተወጥሮም፤ ብዙ አንጸባራቂ ድሎችን አስመዝግቧል። ለእኒህ ድሎች መከተል ዋነኛው ምክንያት፤ ከፊሉ የቅንጅት አመራሮች በይስሙላው የወያኔ ፓርላማ በመሳተፍ ለመለስ ዜናዊ እና ኩባንያው ህጋዊነትን ከማጎናጸፍ ይልቅ የሚመጣውን ሁሉ ለመቀበል ቆርጠው መቆማቸው ነው።

---

[11] ወያኔ ይህ ሁኔታ በግልጽ እንዲታይ በማሰብ ያደረገው ጫና መጠኑን አለፈና ግን፤ ያልታሰበ ውጤት ሊከተል ቻለ። በወያኔ ጸጥታ ወኪሎች አማካይነት በቅንጅት መሪዎች ላይ ይደረግ የነበረው ብልግና፤ ለመሪዎቹ በመጨረሻው ላይ ብዙ ምርጫ አልተወላቸውም። የነበሩት አማራጮች፤ ሊቀበሉት ከማይቻል ውርደት እና የወያኔን ፓርላማ በመፈንገጥ መሀል ያሉ ምርጫዎች ብቻ ሁነው ነበር የቀሩት።

[12] ስለ ሰላማዊ እና ህጋዊ ትግል በዚያን ወቅት ይለፈፍ የነበረው ከትግሉ አንጻር ርባና ሊኖረው ይችል የነበረው፤ ሰበካው ሌላ የትግል ስልት እስኪቀረጽ ድረስ ለጊዜ መግዢያነት የሚያገለግል ታክቲክ ቢሆን ብቻ ነበር። ሌላው ሁሉ ቀልድ ነው።

አንኳሮቹ የግንቦት 97 ህዝባዊ እንቅስቃሴ ድሎች የሚከተሉት ናቸው፡፡

1) ቁጥር ስፍር የሌለው ህዝብ ስለ መብቱ መከበር መነሳሳቱ፤
2) ህዝቡ ‹እንመራሃለን!› እያሉ በሚቀርቡት አካላት ላይ ተጽእኖ የመሳደር ተለምዶ ማግኘቱ፤
3) በሀገራችን የዴሞክራሲያዊ ስርአትን ለማስፈን ለሚደረገው ትግል በጣም አስፈላጊ የሆነው በውጭ ሀገር ወስጥ የሚኖሩትን እና በሀገር ውስጥ ያሉትን ኢትዮጵያውያን ሙሉ ትብብር የሚደረጅበት ሁኔታ መፈጠሩ፤
4) የተቃውሞው እንቅስቃሴ ጠባብ በሆነ ነገር ግን ብዙ ህዝብን ማሳተፍ በሚችል የህግ የበላይነት እና የመብት መከበር ጥያቄ ዙሪያ መተባበር የሚችልበት ሁኔታ መፈጠሩ፤
5) የኢትዮጵያ ተቃዋሚዎችን እንቅስቃሴ ላለፉት 15 አመታት ተብትቦ አላነቃንቅ ብሎ ይዞት የኖረው የመሪነት ጥያቄ በማያሻማ መንገድ ምላሽ ሊያገኝ የሚችልበት ሁኔታ መፈጠሩ፤
6) የተቃዋሚውን ወገን ክርክር የተቀበሉ እና የሚደግፉ የውጭ ሀገር ፖለቲከኞች እና የተለያ ተቋማት መገኘታቸው፤
7) በወያኔ መንግስት በማንአለብኝነት የሚፈጸመው የሰብአዊ እና ዴሞክራሲያዊ መብቶች ጥሰት ለአለም ህዝብ መጋለጡ፤
8) ወያኔ በስልጣን ላይ ለመቆየት ሲል በኢትዮጵያ ህዝቦች መሀል ዘርን መሰረት ያደረገ ጥላቻ እንዲስፋፋ የሚጥር አካል መሆኑ በገሀድ መውጣቱ፤
9) ወያኔ ለ15 አመታት ስለ ህገ-መንግስት እና ዴሞክራሲ ሲያላዝን የኖረው ሁሉ፤ የውጭ መንግስታትን ለማጭበርበር መሆኑ መጋለጡ፤
10) የወያኔ ቅጥፈት እና ክህደት በመጋለጡ ምክንያት፤ በስልጣን ላይ ለመቆየት ጠባብ በሆነ የዘር መሰረት ላይ ከመቆምና ከመሳሪያ ሀይል ውጭ ሌላ ምንም ነገር የሌለው እንዲሆን መደረጉ፤
11) መለስ ዜናዊ ታላቅ የፖለቲካ ሰው ለመባል ሲል ሲሸምነው የኖረው የውሸት ካብ ሁሉ ብጭቅጭቁ መውጣቱና በንጹህ ፋሺስትነቱ ርቃኑን መቆሙ ናቸው

ከላይ የተገለጹት እኒህ 11 የድል ነጥቦች የዴሞክራሲያዊ ትግሉን አንድ እመርታ ያዘለሉት መሆናቸውን የኢትዮጵያ የተቃውሞ እንቅስቃሴ ሲከታተል የኖረ ሰው ሁሉ በግልጽ ይረዳዋል ብለን እናስባለን፡፡ ባሁኑ ወቅት፤ በተለያዩ ጥቅማ ጥቅሞች ተገዝተው ስለ ወያኔ ጸጋ የየመንግስታቶቻቸውን እይታ አሳስተው ይኖሩ የነበሩት የፈረንጅ ተላላኪዎች ቢያንስ አደባባይ ከመውጣት አፍረው ይገኛሉ፡፡ ባሁኑ ወቅት በየምእራብ ሀገሩ ፖለቲካ ተቋም አካባቢ የሚታየው ልምምጥ፤ የአሜሪካ ቡችላነትን ሙጥኝ ብሎ የቆመ ብቻ ነው፡፡ ይህ ደግሞ፤ በቅርቡ ብትንቱ ባይወጣ እንኳን፤ ዘሬ በስልጣን ላይ የሚገኙት የአሜሪካ እብዶች እና ደናቁርት በጥቂት ወራት ጊዜ ውስጥ ከመድረኩ በንነው ሲጠፉ አብሮ የሚበተን ይሆናል፡፡

በተቃዋሚው ወገን ያለውን ሁኔታ ባንጻሩ ብንመለከተው ደግሞ፤ እንቅስቃሴው ታላቅ የህዝብ መሰረትን ይዞ እና የአመራር ጥያቄን መልሶ ለመንቀሳቀስ የሚችልበትን ሁኔታ አሟልቶ ይገኛል፡፡ ከዚህም አልፎ፤ ከአሁን በፊት አይን ለአይን መተያየት አይችሉ በነበሩ በተለያዩ ጎራዎች ውስጥ በሚገኙ የተቃውሞ እንቅስቃሴዎች መሀል ልዩነቶችን በማቻቻል አብሮ የመንቀሳቀስ ፍቃደኛነት የሚታይበት ወቅትም ነው፡፡

ስለዚህ፤ በጥቅሉ ወቅቱ የተቃዋሚዎች ጎህ የቀደደበት የወያኔ ቀን የመሸበት ሁኖ ቢታይ ትክክለኛ ነው፡፡ ይህ የተቃዋሚው ወገን የበላይነት በአብዛኛው የሞራል ድል፣ ሰፊ የህዝብ ድጋፍ ስሜት፣ አዎንታዊ የሆነ የዲፕሎማሲ ሁኔታ፣ ህዘብን ያስመረረ ሃገራዊ የአፈናና የኑሮ ውድነት ሁኔታ ጋር የተሳሰረ ነገር ግን ቁሳዊ ልባሰ የሚያንሰው መሆኑን መረዳት ያስፈልጋል፡፡ በተባለው የበላይነት ሁኔታ ላይ በአግባቡ በፍጥነት ካልተሰራበት እና ካልተገነባበት ግን፤ ዘላቂነት የማይኖረው ነው፡፡ እንዲያውም፤ እንዲህ አይነቱን ዳተኛነት ወያኔ የመሳሪያ፤ የገንዘብ እና የድርጅት ጥንካሬውን ተጠቅሞ ወደ ራሱ ጠቀሜታ ጊዜ ሳይፈጅበት ሊለውጠው የሚችል ይሆናል፡፡ በመሆኑም፤ ማንኛውም ስለ ሀገሩ በጎ የሚያስብ ሰው ሁሉ በቅድሚያ ሊያነሳ እና ሊመልሰው የሚሞክረው አብይ ጉዳይ፤ ‹ትግሉን ወደፊት ለማራመድ ምን መደረግ አለበት?› የሚለውን ብቻ መሆን አለበት፡፡ ሌለው በመሉ ከእዚህ አብይ ጥያቄ ምላሽ በኋላ የሚከተል ነው፡፡

**4- የዴሞክራሲን ትግል ወደፊት ለማራመድ ምን መደረግ አለበት?**

ለዚህ ጥያቄ የሚሰጠው አጠቃላይ መልስ በሚከተሉት ሶስት ፈርጆች ሊመደብ የሚችል ነው።

1) ***ትግሉ ያቀናጀንን ድሎች በጽኑ መሰረት ላይ እንዲቀመጥ ማድረግ፤*** -ከላይ እንደተዘረዘረው የግንቦት 97ቱ ህዝባዊ እንቅስቃሴ፤ አመራርን፤ ህዝባዊ ተሳትፎን፤ ህዝብ በመሪዎቹ ላይ ተጽእኖ ማሳደር መቻሉን፤ ዴሞክራሲያዊ የአሰራር ስልቶችን እና የነጻ ሀሳብ ሽርሽርን የመሰሉ አዎንታዊ ድሎችን አስጨብጦናል። እኒህ ድሎች በተናጠል በየስፍራው አቆጥቁጠው የሚታዩ እንጂ፤ በጽኑ መሰረት ላይ የተቀመጡ ስላልሆኑ፤ ይህንን ጉድለት ለማሟላት ያላሰለሰ ጥረትን ማድረግ ያስፈልጋል። እኒህ ጥረቶችም እንደየአግባቡ ለድሎቹ ተቋማዊ ቅርጽን መስጠት እና/ወይም ዴሞክራሲያዊ እና ህዝባዊ እምነቶች በእያንዳንዱ ልቦና ውስጥ በጥልቀት የሚሰርጹበትን መንገድ ማፈላለግ[13] እና መግፋት ናቸው።
2) ***የተጋለጡት የወያኔ ድክመቶች ተመልሰው እንዳይሸፈኑ ማድረግ፤*** -የወያኔ ስርአት በሙስና የበከተ፤ ጸረ ህዝብ፤ ጸረ-ኢትዮጵያ፤ ነፍሰ ገዳይ፤ ወሮበላ፤ አጭበርባሪ፤ ዘረኛ እና አምባገነን መሆኑ በትግሉ ምክንያት ግልጽ ወጥቷል። መመልከት ለፈለገ ማለታችን ነው። ወያኔ የተጋለጠባቸውን ጉዳዮች ምንም የማያወዛግቡ ሁነው ቢገኙም፤ ስርአቱ የጨበጠውን የገንዘብ እና ድርጅታዊ አቅም መሳሪያ በማድረግ ያንን ምስሉን ለመቀልበስ ከመሞከር አልቦዘነም። እንደ ወያኔ እና አንዳንድ በጥቅም የተገዙ በምእራብ ሀገሮች ውስጥ የሚገኙ ተላላኪዎቹ ቢሆን ኑሮ፤ ይህ ሂደት ተጠናቅቆ ነገሩ ሁሉ በአሁኑ ወቅት እንደ ቅድመ 97ቱ አልጋ በአልጋ በሆነ ነበር። ነገር ግን፤ በውጭ ሀገር የሚኖሩት ኢትዮጵያውያን በጣም አስቸጋሪ በሆነ ሁኔታ ውስጥ ተገኝተውም ቢሆን ባደረጉት ትግል ይህ የወያኔ ጥረት እስካሁን ምንም ውጤት ሳያመጣ ቀርቷል። ይህ የወያኔ ጥረት ግን ከህልውናው ጋር የተያያዘ በመሆኑ፤ በዚህ አንጻር ወያኔ የማይፈነቅለው ደንጊያ አይኖርም[14]። ወያኔ/መለስ[15] ደርግን ለመጣል በሚሯሯጥበት ወቅት፤ ያልሰገደበት የውጭ ሀገር መድረክ አልነበረም። በዚያውም መጠን ወደ መንግስታቱ ተቋማት አደባባይ ሊያደርሱ የሚችሉ የአይጥ መንገዶችን ያውቃል። እኒህ መንገዶች እንዳይዘጉም ጥገኞቻቸው እና እነርሱም ራሳቸው እንደ መንግስት ከኢትዮጵያ ህዝብ እየመጠመጡ የሚወስዱትን ሀብት በመጠቀም፤ በየጊዜው ለሞሰኑ ተላላኪዎቻቸው የሚፈልጉትን ሁሉ ሲያቀርቡ ኑረዋል። ከቅርብ ጊዜ ወዲህ ደግሞ የተማጽእኖ ኩባንያዎችን አገልግሎት በብዙ ገንዘብ እየገዙ ሲንቀሳቀሱ ይታያሉ። ስለዚህ በዚህ አንጻር የሚደረገው ትግል፤ ከመቼውም ጊዜ የበለጠ የሰላ እና የተቀነባበረ ሊሆን ይገባዋል። በአግባቡ ከተሰራበት እና ከታሰበበት[16]፤ ይህን ሁሉ በሙስና እውነትን ለመሸፋፈን የሚደረግ መግበስበስ በቀላሉ መበታተን ይቻላል። ይህንኑ ርእስ ከመልቀቃችን በፊት፤ ከዚህ ውጭ ደግሞ ሊታሰብበት የሚገባ አንድ አቢይ ጉዳይ ደግሞ፤ ወያኔን ለመቋቋም ሲባል የሚደረገው ትግል በዙሪያው የተሰባሰቡትንም ሆነ ለወደፊቱ ሊሰባሰቡ የሚችሉትን አካላት እንዳይከፋፍል ልዩ ጥንቃቄ ማድረግን ነው።[17]

---

[13] ስነ ጽሁፍ፤ ሙዚቃ፤ ድራማ፤ ራዲዮ፤ ጋዜጣ፤ በሀይማኖት አባቶች የሚደረጉ ስብከቶች እና የመሳሰሉት ሁሉ ከዚህ አንጻር ከፍጸኛ ሚና ሊኖራቸው የሚችሉ ናቸው።

[14] በእነ ኤፍሬም ይስሀቅ መሪነት ‹እርቅ› እየተባለ የሚሰበክለት ፊሽካ የዚህ ስትራቴጂ አካል ሊሆን እንደሚችል መጠርጠር ተገቢ ነው።

[15] የመለስ ዜናዊን ‹በእናቴ አረብ ነኝ!› ታሪክ ያልሰማ ይኖራል፤ ብለን አንገምትም።

[16] ወያኔን ዘመቻ ለመግታት ሲባል በጃፍሬዚ እና ያማሞቶ አካባቢ የወጣው ልፋት፤ ለፍትህ ጥብቅና በመቆም ጥያቄ ውስጥ ሊገቡ በማይችሉ አካባቢዎች ቢዘራ ኑሮ የአሜሪካንን ውጭ ጉዳይ ሚኒስትሮች እይታ መለወጥ ባንችል እንኳን ንግግራቸው ራሱ በማንአለብኝነት የማይወረወር ለከተቢስ እንዳይሆን ማድረግ እንችል ነበር። ወደ ምእራብ መንግስታት የስልጣን አደባባይ ሊያደርሱ የሚችሉ ከሞራላዊ ቁመናችን ጋር የማይጻረሩ የተለያዩ መንገዶችን በትጋት ማጥናት እና መጨበጥ ያስፈልጋል።

[17] ይህንን ነጥብ አጉልቶ ለማሳየት በምሳሌነት አንዳንድ ነገሮችን ማቅረቡ ይጠቅም ይሆናል። ለሚላንየም ወደ ሀገራቸው ገብተው ከዘመዶቻቸው ጋር በአሉን ለማክበር የፈለጉ ኢትዮጵያውያንን እንደ ጠላት ፈርጆ መኮነን ስሜታዊነት ነው። ወያኔ ዘርን መሰረት ባደረገ አቅጣጫ ብዙ ሰዎችን አወናብዶ ተቃዋሚውን እንዲፈሩ ያደረጋቸው አሉ። በእርግጥ አንዳንዱ ደግሞ የወያኔ ካድሬም ሊሆን ይችላል። ከእኒህ አይነት ግለሰቦች ጋር በማንኛውም ስፍራ እና ቦታ በሚደረግ ግጥሚያ እና ፍጥጫ ውስጥ ከእነርሱ ተመሳሳይ በሆነ መንገድ መነጋገር እና መመላለስን በማስወገድ ጨዋነትን የተላበሰ ባህርይ ማሳየት አስፈላጊ ነው። እንዲህ አይነቱ አካሄድ ከሞራል ቁመና አንጻር ብቻ ሳይሆን የሚደገፈው፤ ለትግሉ አጋር ሊሆኑ የሚችሉ ሰዎችን ሁሉ ለማረጋጋት እና ለማስተባበርም የሚጠቅም የትግል ስልት አካል ነው።

3) ***<u>የቀረውን የወያኔን ጠንካራ ጎን ማወላለቅ፤-</u>*** በግንቦት 97ቱ እንቅስቃሴ ሳቢያ ወያኔ የፖለቲካ እና ማህበራዊ ልባሱን ተገፍፎ ርቃኑን የቆመ የሞሰነ ወታደራዊ ሀይል ሁኖ ይገኛል። ለወያኔ መጠንከር አጋዥ ሁነው የሚገኙት ሁኔታዎች በዝርዝር ሲቀመጡም፡--ሀ) የወታደራዊ እና የስለላ ሀይል፤ ለ) የገንዘብ አቅም፤ ሐ) በዘረኛነት ላይ በተመሰረተ አወናባጅ ቅስቀሳ ምክንያት ለደህንነቱ በመስጋት ከወያኔ ዙሪያ የተሰለፈ የሰው ሀይል፤ መ) ከወያኔ ጋር በመጠጋት ብዙ ጥቅማ ጥቅሞችን የሚቦጠቡጡ ኢትዮጵያውያን እና በእነርሱ ዙሪያ የተሰበሰቡ ተደኅሚዎች፤ ሠ) ተራ በሆኑ አልባሌ እና ወራዳ ጥቅሞች ተተብትበው በሚገኙ የአንዳንድ የውጭ ሀገር ተወላጆች፤ ጋዜጠኞች፤ ፖለቲከኞች እና ዲፕሎማቶች አማካይነት የምእራብ መንግስታትን እይታ ለመበረዝ የሚደረግ የልምምጥ አቅም፤ ረ) በሀገር ጥቅም ኪሳራ ለውጭ መንግስታት አገልጋይነት ከወያኔ የተሻለ እንደሌለ አድርጎ ማቅረብ፤ ተብለው ሊጠቀሱ ይችላሉ። ስለዚህ የወያኔን ጥንካሬ ለማወላለቅ ከላይ በተዘረዘሩት እያንዳንዳቸው ጉዳዮች አንጻር አግባብነት ያላቸው ስልቶች መቀየስ አለባቸው። በሀገራችን ዴሞክራሲያዊ ስርአትን መገንባት የምንፈልግ ወገኖች፤ በዚህ የተቀደሰ አላማ ዙሪያ ሊሰባሰብ የሚችለውን ሁሉ ማስተባበር ስለሚኖርብን፤ ከወያኔ ከድተው ከህዝብ ጋር ሊቆሙ ለሚችሉ አካላት ሁሉ መድረካችንን አዘጋጅተን መጠበቅም አለብን። እኒህ ስድስት ጉዳዮች እያንዳንዳቸው በጥንቃቄ ተጠንተው ከሌሎች የትግሉ ጉዳዮች ጋር ተቀናጅተው ተቀርጸው ሊካሄዱ የሚገባቸው ናቸው። በመሆኑም ብዙ ዝርዝር ጉዳዮችን እና አካሄዶችን የሚጠቀልሉ በመሆናቸው ለወደፊቱ እየተስፋፉ እና እየተብራሩ ይቀመጣሉ። በዚህ ጽሁፍ ክልል አንጻር ግን በስራ ላይ ልናውላቸው የሚችሉ ሃሳቦች መኖራቸውን መግለጹ በቂ ነው።

4) ***<u>የትግሉን ደካማ ጎኖች ማረቅ እና ማስተካከል</u>***፤--ከላይ የተዘረዘሩትን ጉዳዮች ሁሉ ከትግሉ ደካማ ጎንነት አንጻር መተርጎም እና መመልከት ይቻላል። እኒዚያ ጉዳዮች ግን በየተመደበላቸው ስፍራ በዝርዝር የሚተነተኑ ስለሆነ፤ በዚህ ንኡስ ርእስ ስር ልናተኩርበት የምንወድደው ጉዳይ ጥቅል የሆነውን፤ ከስራ አመራር ጉድለት የሚመጣውን ችግር ነው። ቀደም ብለን እንደገለጽነው፤ የግንቦት 97ቱ እንቅስቃሴ በማናቸውም የድራማው ተዋናይ ዘንድ ባልታሰበ መንገድ የህዝብን መብት ጉዳይ በኢትዮጵያ ፖለቲካ መድረክ ላይ አውጥቷል። በዚያው መጠን ከዚህ ቀጥሎ የሚኬድበት ሁኔታ በወያኔ ሙስና፤ የስልጣን ጥመኛነት የዘረኛነት ፖለቲካ ምክንያት መራር እንደሚሆን ይገመታል። ስለዚህ፤ ለተቃዋሚው ወገን በኢትዮጵያ ለውጥን ከማስከተል አንጻር ያለው ምርጫ ሁለት ብቻ ነው። አንደኛው አፍን ዘግቶ በመቀመጥ ከወያኔ ዝርፊያ የሚንጠባጠበው ለሀገር እድገት እንዲጠቅም መመኘት፤ ቢቻልም ዲፕሎማሲያዊ፤ ቴክኒካዊ እና ፖለቲካዊ ድጋፍን መስጠት ነው[18]። ሌላው አማራጭ ደግሞ፤ ወያኔ የህግ የበላይነትን የህዝብን ሉአላዊነት እንዲቀበል ማስገደድ፤ እምቢ ካለም ማስወገድ ነው። በእኒህ ሁለት ምርጫዎች መሀል የሚደረግ አካሄድ ሁሉ፤ ህዝብን እና ራስን የሚያስመታ ስለሆነ ለሴኮንድ እንኳን ልናስብበት አይገባም። ከላይ እንደገለጽነው ታላቁ የዚህ እንቅስቃሴ ድል፤ የቅንጅት አመራር በመርህ ደረጃ በሁለተኛው ሰርጥ ለመሄድ መወሰኑ ነው። በዚህ አቅጣጫ እስካሁን የተደረገው እንቅስቃሴን ከተመለከትን ግን፤ በአካሄድ ዝርክርክነት የተነሳ ከጫጫታ ያለፈ የተመዘገበ ብዙም ነገር የለም። ስለዚህ፤ የትግሉን ድክመት ለመወጣት የሚያስፈልገው የመጀመሪያ እና ተቀዳሚ ጉዳይ፤ ይህንን ዝርክርክነት ለማረም መወሰድ ያለበት ቀዳሚ እርምጃ ምን እንደሆነ ማወቅ እና መፈጸም ነው። በእኛ እምነት፤ ከዚህ አንጻር ሁለት መታረም ያለባቸው ድክመቶች ቅድሚያን ያገኛሉ። እነርሱም፤ ሀ) ትግሉ በደረሰባቸው ደረጃዎች የጠየቃቸውን የአደረጃጀት ቅርጾች አለማሟላት፤ ለ) ዋነኛ የትግል ስልት አቅጣጫን ወቅታዊነት ባለው ሁኔታ አለመቅረጽ ናቸው። በአደረጃጀት በኩል

---

[18] በየነ ጴጥሮስ እና ልደቱ አያሌው። በየነ ግንቦት 97 ላስነሳቸው መሰረታዊ የዴሞክራሲ ጥያቄዎች ምላሽ እንዲገኝ ለመታገል ድፍረቱን በማጣትና ጥቅሙን በማሰላሰል፣ "ልጅ የያዘውን ይዞ ያለቅሳል" በማለት ፓርላማ ገብቶ የወያኔ አጃቢ ሆነ። ነገር ግን የያዘውን ተቀመቶ የሚያለቅስበትንም መብት አጥቶ ተቀምጧል። ሂሳዊ ድጋፍ በሚል ብልጣብልትነት ከወያኔ ጉያ ለመሸጎጥ የሞከረው ልደቱ አያሌውም ተቃወሚዎች ፓርላማ ገብተዋል ብሎ ወያኔ የሚፏልልበትን ተጨማሪ የዲፕሎማሲ ሽፋን ከሰጠና ለዴሞክራሲ ሃይሉ መመታት አስተዋጽኦ ካደረገ በኋላ ዴሞክራሲ በእዚህ ሃገር የለም ለማለት ሲዳዳው ሰምተናል:: በተለይ አሁን የቀበሌና የወረዳ ምርጫ በማለት ወያኔ ሃገሪቱን ቀድሞ ሞዴል አድርጎ ሲያያት በነበረችው ኮምኒስት አልባኒያ ምስል ለመቅረጽ በእብሪት ሲንቀሳቀስ እያየ በእዛ ሀገር ውስጥ ፓርላማ በመቀመጥ የዴሞክራሲን ስራ እየሰራሁ ነው የሚል አይና አውጣ ይኖራል ብለን አንገምትም።

የታየው ጉድለት በአሁኑ ወቅት ለሁሉም የታየ በመሆኑ፤ ብዙም አያነጋግርም። ጤነኛ አእምሮ ሊስተው የማይችለው ጭብጥ፤ በሀገር ውስጥ ብዙ ህዝብን ያሳተፈ ግልጽ እና ህጋዊ እንቅስቃሴ ማድረግ አለመቻሉን ነው። ልብ ያለው ሁሉ ልብ ሊያደርግ እንደቻለው፤ ወያኔ ለፖለቲካ ድርጅቶች እንቅስቃሴ የግልጽነት ፈቃድ የሚሰጠው ለስለላ ስራው እንዲያመቻቸው ብቻ እንጂ፤ ለእንዲህ አይነት አሰራር እና መብት አክብሮት ስላለው አይደለም። ከምርጫ 97 ወዲህ በመልካም አስተዳደር ስም በየቦታው እየተደረገ ያለው ምሽግን የማጠንከር ስራ የሚያመለክተውም፤ ከአሁን ወዲያ እንደ 97ቱ አይነት ሙከራ ቢመጣ ወያኔ ሁኔታውን ለመቆጣጠር የሚያስችለውን አቅም እያካበተ መሆኑን ነው። ይህ እይታ በራሱ አወዛጋቢ ባይሆንም፤ የእንቅስቃሴውን መንፈስ እና ይዘት በተመለከተ ግን፤ አንዳንድ ጎራባጭ ነገሮችን በአእምሮአችን ውስጥ የሚፈጥር መሆኑን መካድ አይቻልም። እኒህም ጉዳዮች፤ ምንም እንኳን የግልጽነት አሰራር ዴሞክራሲያዊ ስርአትን ከመመስረት አኳያ ከፍተኛ ዋጋ የሚሰጠው ባህል መሆኑ ባይካድም፤ በወያኔ መሰሪ ስርአት ምክንያት ምርጫችን በህቡእ አደረጃጀት ትግሉን ማራመድ ወይም ለወያኔ በደል ተንበርክኮ መኖር ብቻ ናቸው። ምርጫችን ቀደም ብለን እንደገለጽነው ለወያኔ በደል አለመንበርከክ በመሆኑ፤ ከአደረጃጀት አንጻር የምንወስደው አማራጭ የሌለውን የህቡእ አደረጃጀት መሆን ይኖርበታል። እንዲህም አይነት አማራጭ የሌለው ምርጫ ብንወስድም ግን፤ ልንቀዳጀው ያሰብነውን የዴሞክራሲያዊ ስርአት እምነቶች በጣም አስቸጋሪ በሆኑ ሁኔታዎችም ውስጥ ሁነን ጠብቀን የምንሄድበትን ሁኔታ ማመቻቸት ይኖርብናል። ይህም በተባለው የህቡእ መንገድ ተደራጅተው ለመንቀሳቀስ ውሳኔ በሚያደርጉ ተቃዋሚ ድርጅቶች ውስጠ ደንብ እና ህግ ውስጥ የሚካተት እና ልእልናን የሚያገኝ መሆን አለበት ብልን እናምናለን። የወያኔን ዘመን የሚያውቅ ኢትዮጵያዊ ሁሉ እንደሚረዳን__ግን፤ እንዲህ ያለ ከዴሞክራሲ ጋር የተዛመደን አቢይ ጉዳይን በወረቀት ላይ በተቀመጠ ህግ ዋስትና መተው አይቻልም፡ በሁሉም ተቃዋሚ ድርጅቶች ውስጥ ነጻ የሀሳብ መሸራሸር እና ዴሞክራሲያዊ አሰራር ለመኖራቸው ዋስትና ሊሰጡ የሚችሉ ተቋማዊ መጠብቆችን ማደራጀት ተገቢ ይሆናል። ከዚህም አንጻር የሚከተሉት መርሆዎች ጠቀሜታ ይኖራቸዋል ብለን በማመን አቅርበናቸዋል።

ሀ) በውጭ ሀገሮች ውስጥ ያለውን የእንቅስቃሴውን ክንፍ በተጀመረው መልኩ በግልጽ እና በገሀድ ማደራጀት፤ በተቻለ መጠን ጭፍን የግለሰቦችና የቡድኖች ደጋፊነት ባህል እንዲወገድ በማድረግ እንቅስቀሴው በሃገራችን የዴሞክራሲ ስርአት ግንባታ ላይ ባተኮሩ ጉዳዮች ላይ መሰባሰብና መተባባር የሚፈልገውን በሙሉ አካቶ የሚሄድ ሰፊ መሰረት ያለው በሩቁ አልሞ የሚያድር እንቅስቃሴ ማድረግ።

ለ) በሀገር ውስጥ የሚኖረውን የህቡእ አደረጃጀት በውጭ ሀገር ከሚኖረው ግልጽ አሰራር ጋር ማቀናጀት፤

ሐ) በህቡእ በሀገር ውስጥ የሚደራጅ መዋቅር አካላት በግልጽ የተደራጁትን የውጭ ሀገር መዋቅር አካላት ሊገናኙ የሚችሉባቸውን የተለያዩ መገናኛ ዘዴዎች ማመቻቸት እና በድርጅቱም የውስጥ አስተዳደር ስርአት እና ደንብ ውስጥ ማካተት[19]፤

መ) የኦዲት እና ቁጥጥር ኮሚቴ የመሳሰሉ ድርጅታዊ አካላት ነጻ በሆነው በውጭ ሀገር ውስጥ እንዲቋቋም እና እንዲሰራ ማድረግ፤

ሠ) ቅንጅት በአሁኑ ወቅት በሀገሪቱ ውስጥ ከሁሉም ተቃዋሚ ድርጅቶች የላቀ ተከታይ እና ድጋፍ ያለው ድርጅት ቢሆንም፤ ራስን ከሁሉ በላይ የገዘፈው የህዝቡ እንቅስቃሴ[20] አንድ አካል ብቻ አድርጎ በመመልከት ላይ የሚመሰረት፤ ለጋራ አላማ የተሰለፉ ወገኖች በሙሉ የሚሳተፉበት ዘርፈ ብዙ ታላቅ የትግል ህብረት መፈጠርን የሚያስችል ድርጅታዊ መዋቅር እንዲይዝ ማድረግ፤

ረ) ዘርፈ ብዙ ለሆነው የትግል ህብረት ከሁሉም ድርጅቶች አባልነት ነጻ የሆኑ፤ ነገር ግን በጨዋነታቸው እና በአስተዋይነታቸው በሁሉም ወገኖች ዘንድ ተቀባይነት ያላቸው የሀገር

---

[19] በርግጥ እንዲህ ሲባል ደግሞ፤ እንዲህ አይነቱ መቀናጀት ለወያኔ ስለላ የሚከፍተውን ምቹነት መዘንጋት አይገባም። የመገናኛ ስርአቶች እና መስመሮች ሁሉ ዘርዘር ባለ ጥናት መሰረት የሚፈጸሙ መሆን ይኖርባቸዋል።

[20] በአሁኑ ወቅት የሚታየው፤ የህግ የበላይነት እና የዴሞክራሲያዊ ስርአት ምስረታ ለዚህ እንቅስቃሴ ማመላከቻነት በቂ ናቸው።

ሽማግሌዎች የእንቅስቃሴው አዲት ኮሚቴ አባላት ሁነው መስራት ስለማስፈለጋቸው የጋራ ስምምነት ላይ እንዲደረስ ማድረግ።

እንቅስቃሴውን ወደፊት ለማራመድ የሚያስፈልገውን አደረጃጀት ጉዳይ፣ ከላይ እንደተዘረዘረው ካስቀመጥን በኂላ የሚቀረን አቢይ ጉዳይ አግባብ ያለውን ዋነኛ የትግል ስልት መወሰን ነው። ከሁሉ አስቀድሞ፣ በቅንጅት ተይዞ የኖረው የሰላማዊ ትግል ስልት እንደገና መመርመር ይኖርበታል።

## 5- ሰላመዊ የትግል ስልት ሲመረመር

በዚህም አንጻር ሰላማዊ ትግል ስንል ምን ማለታችን ነው? የሰላማዊ ትግል ጸጋ ምንድን ነው? ሰላማዊ ትግልን ለማካሄድ ምንስ ቅድመ ሁኔታ መሟላት አለበት? ሰላማዊ ትግልን ካካሄዱ ሀገሮች ተለምዶ ምን ትምህርት እንቀስማለን? ሰላማዊ ትግልን ሞክረው የከሸፈባቸው ሀገሮችስ አሉ ወይ? ካሉስ ትግሉ እዚያ እንዴት ሊከሽፍ ቻለ? ይህ ሁሉ የሰላማዊ ትግል ዘገባ በሀገራችን ሁኔታ ሲተረጎም ምን ይመስላል? ከዚህስ በመነሳት በሀገራችን ሰላማዊ ትግልን በአሁኑ ወቅት ማካሄድ እንችላለን ወይ? ሰላማዊ ትግልን በአሁኑ ወቅት ማካሄድ ካልተቻለስ በሌላ ወቅት ወደርሱ መመለስ ይቻላል ወይ? ያ ወቅትስ መቼ ነው? ምንስ ሁነታዎች ተሟልተው ሲገኙ ሊከተል ይችላል? ሁኔታዎች እንዲሟሉ ለማድረግስ በእኛ በኩል ልናደርጋቸው የሚገቡ ነገሮች ምንድን ናቸው? የሚሉት ጉዳዮችን መዳሰስ ተገቢ ነው።

በአንድ የፖለቲካ ድባብ ውስጥ የሚኖሩ የተለያዩ ወገኖች ስለ ጋራ እድላቸው የተለያዩ እይታዎች ይኖሯቸዋል። እኒህንም እይታዎች በፖሊሲ መልክ ቀርጸው ለመተርጎም በሚነሱበት ወቅት፣ የጥቅም ግጭቶች ይፈጠራሉ። ድባቡ እንዲህ አይነት ልዩነቶችን ማስተናገድ የሚቻልባቸው ስርአቶችን እና ተቋማትን አዘጋጅቶ የተገኘ ከሆነ፣ ልዩነቶቹ ውድመት እና እልቂት ሳያስከትሉ ፖሊሲዎች የሚስተናገዱበት ሁኔታ ይከተላል። ሂደቱም ሰላማዊ ትግል ይባላል።

ዴሞክራሲያዊ ስርአቶችን ከዚህ አንጻር ስንመለከታቸው፣ እንዲህ አይነት ልዩነቶችን ለማስተናገድ በአሁኑ ዘመን ከሚገኙ ማናቸውም ስርአቶች ሁሉ የላቀ ብቃት እና አቅም እንዳላቸው አድርገን መውሰድ እንችላለን። በዴሞክራሲያዊ ስርአቶች ውስጥ ማንኛውም ፖሊሲ የህዝብን ጆሮ አግኝቶ በአብዛኛው ህዝብ ድምጽ እስከተደገፈ ድረስ ሊስተናገድ የሚችልበት ስርአት ተመቻችቶ ተቀምጧል። ይህ አሰራር ከስርአቱ ተነጥሎ ሊታይ የማይችል ባህርይ ነው። አንድ ስርአት ዴሞክራሲያዊ ባይሆንም ግን፣ ከዚያ መለስ ያሉ እንዲህ አይነት ልዩነትን ለማስተናገድ የሚያስችል መሆን ይችላል። ዴሞክራሲያዊውም ሆነ እንዲህ አይነቱ ሌላ ስርአት እንዲህ አይነት በሰላማዊ መንገድ ልዩነትን ለማስተናገድ እንዲችል ግን አንድ ቅድመ ሁኔታ እንዲኖር ግድ ነው። እርሱም፣ ከተቀናቃኞቹ ቁመና በላይ ገዝፎ የተቀመጠ አካል የመገኘቱ ጉዳይ ነው። ህግ፣ እግዚአብሄር፣ ከፖለቲካ በላይ የሆነ ንጉስ ወዘተ… የመሳሰሉት ሁሉ በህብረተሰቡ ውስጥ ልእልናን የተቀዳጁ ከሆኑ የእንዲህ አይነቱ አካል ተደርገው ሊወሰዱ የሚችሉ ናቸው።

እንዲህ አይነቱ ሁኔታ በሌለበት ድባብ ውስጥ የሰላማዊ ትግል መንገድ አስፋልት ሳይሆን፣ ገረጋንቲ እና ኮረኮንቻም ብቻ ነው። እንደ መንገዱም አስቸጋሪነት እየተላላጡ ከግብ ሊደረስ ወይም በየሾለው ደንጊያ ላይ ተቸንክሮ ሊቀር ይቻላል።

ሰላማዊ የትግል ስልት ስኬታማ እንደሆነ በምሳሌነት ከሚጠቀሱት ሀገሮች ውስጥ የጋንዲዋ ህንድ እና በቅርቡ ደግሞ የምስራቅ አውሮፓ ሀገራት ቅድሚያውን ይዘው ይገኛሉ። ከእዚህ ውጭ በሰላማዊ ትግል ስኬታማነት የሚጠቀሱ በየሃገሩ የተደረጉ የሲቪል መብቶች እንቅስቃሴዎች አሉ። ከእነዚህ እንቅስቀሴዎች መሃል በኢትዮጵያውያን አካባቢ በስፋት ሲጠቀስ የምንሰማው በአሜሪካ የሚገኙ አፍሪቃዊ አሜሪካኖች በማርቲን ሉተር ኪንግ መሪነት የዜግነት የእኩልነት መብታቸውን ለማስከበር የተደረገው ትግል ነው። የሲቪል መብቶች እንቅስቃሴ የመንግሰት ስርአቱ እንዳለ ሆኖ ለተወሰኑ መብቶች መከበር የሚደረግ ትግል በመሆኑ አጠቃላይ ስርአቱን ስርነቀል በሆነ መንገድ ለመቀየር የስልጣን ሹም ሽር ለማድረግ ወይንም ጠቅላላ ነጻነትን ለማስከበር እንደሚደረገው ትግል በስልጣን ላይ ካለው መንግስትና እሱን ከሚደግፈው የህብረተሰብ ክፍል ከፍተኛ ተቃውሞ አይገጥመውም። ይህ ማለት የጥቁሮችን መብት ለማስከበር የተደረገው ትግልና የተከፈለው

መስዋእትነት ቀላል ነበር ለማለት አይደለም። ፈተናውም ችግሩም በህንድና በምስራቅ አውሮፓ የተለየ ነበር ለማለት ነው። በኢትዮጵያ እየተነሳ ያለው ጥያቄ መሰረታዊ ከሆነው የመንግስት ስልጣን ጋር የተያያዘ በመሆኑ ከህንድና ከምስራቅ አውሮፓ ሀገሮች ተመክሮ ጋር ይቀራረባል። ይህም ተብሎ ግን ከኢትዮጵያው በስተቀር ያቀረብናቸው የሰላማዊ ትግል ምሳሌዎች የጋራ ባህርይ፤ በድባቡ ውስጥ የተወሰነ የህግ ልእልና መኖሩ እና በስልጣን ላይ የነበሩት አካላት የተወሰነ የአርቆ አስተዋይነት እና የሞራል ቁመና በነበረበት ሁኔታ የተከናወኑ መሆናቸው ነው። ከዚህ ውጭ ግን፤ ትግሉ በህንድና በምስራቅ አውሮፓ እንዲሳካ ያደረጉ የተለያዩ ብቸኛ ምክንያቶችም አሉ።

የእንግሊዝ ኮሎኒያሊስቶች በወቅቱ ከሁለተኛው አለም ጦርነት ደክመው ከመውጣታቸውም በተጨማሪ፤ በህንድ ሰላማዊ ትግሉ ቢታመቅ ሊከተል የሚችለውን አደጋ መገንዘብ የቻሉ ነበሩ። በምስራቅ አውሮፓ የነበረው ደግሞ፤ ሀ) ምእራባውያን ለራሳቸው ጥቅም ሲሉ የሰጡትን ከፍተኛ ድጋፍ፤ ለ) የህዝቡን የባህል እድገት ደረጃ፤ ሐ) የተቃዋሚዎቹ አካላትን የድርጅት፤ የዝግጅት እና የገንዘብ አቅም፤ መ) እንቅስቃሴው ባሳደረው ተጽእኖ ምክንያት በመንግስት ተቋማት መሀል የተከተሉ ክፍፍሎችን፤ እና ሠ) መሪዎቹ ስለ ሀገራቸው መጻኢ እድል የሰጡትን አክብሮት የሚያካትት ነው።

ከህንድ እና ምስራቅ አውሮፓ በተጻራሪው ጫፍ የሚገኙት ደግሞ፤ ሰላማዊ ትግል ተሞክሮ የከሸፈባቸው ወይም እስካሁን ድረስ ያልተሳካባቸው ደቡብ አፍሪካን፤ በርማን እና ቲቤትን የመሰሉ ሀገሮች ይገኛሉ። በእነዚህ ሀገሮች ውስጥ ሰላማዊ ትግል ያልተሳካበት ዋነኛ ምክንያት የተቃዋሚዎቹ ሞራልና ቁመና ከገገሮቹ ሳይልቅ ቀርቶ ወይም በታጋዮቹ ድክመት ሳይሆን፤ በመንግስት ስልጣን ላይ የተቀመጡት አካላት ተቃዋሚዎቻቸውን ለመቆጣጠር ሲሉ ምንም አይነት እርምጃ ከመውሰድ ወደኋላ የማይሉ በመሆናቸው ነው።

ቻይና የኮሙኒስት ፓርቲውን መዋቅር እና የአስተዳደር መሳሪያዎችን በመጠቀም፤ በሀገርዋ ውስጥ ምንም አይነት የተለየ አመለካከት ያለው እንቅስቃሴ እንዳይነሳ ሁልጊዜም በተጠንቀቅ ቁማ የምትጠብቅ ሀገር ነች። በመሆኑም፤ የቲቤት ህዝብ መሪ የሆኑት ዳላይ ላማ ከህዝባቸው ጋር እንዳይገናኙ እንኳን ሁነው በስደት ይኖራሉ። በበርማ ደግሞ ስልጣን ላይ ያለው ወታደራዊ አምባገነን መንግስት የዛሬ 15 አመት ገደማ አቆጥቁጦ የነበረውን ሰላማዊ ትግል ሁለ ገብ በሆነ እመቃ ተቆጣጥሮ እየቀጠለ ይገኛል።

የደቡብ አፍሪካው ሁኔታ ግን፤ ከሌሎቹ ሁሉ የበለጠ ከሀገራችን ሁኔታ ጋር ተመሳሳይነት ያለው ነው። ትልቁ ተመሳሳይነት፤ ግዛቱ በዘረኛነት ላይ መመስረቱ ሳይሆን፤ ሰላማዊ ትግል የሚቻልበት ሁኔታ እንዳለ አስመስለው የሚያሳዩ የይስሙላ ተቋማቱ ሁኔታ ነው። በደቡብ አፍሪካ፤ ፓርላማ፤ ምርጫ እና ፍርድ ቤቶች በነጻነት የሚንቀሳቀሱ ሁነው ይታዩ ነበር። ነገር ግን፤ የተቋማቱ ተቀዳሚ ስራ የስርአቱን መለወጥ የሚያስከትሉ ሁኔታዎችን ሁሉ በህግ ከለላ ዘግቶ መያዝ ነበር። በተለይ የህግ ስርአትን በተመለከተ በወያኔ መንግስት እና በደቡብ አፍሪካ በነበረው የጥቂት ነጮች መንግስት መሀል የነበረው ተመሳሳይነት የሚገርም ነው። በዚህ ዘመን፤ የህግ ፍልስፍና መሰረት እኩልነትን ማራመድ ሁኖ ሳለ፤ በደቡብ አፍሪካ የነበረው ህግ ግን የነጮችን የበላይነት አረጋግጦ ለመኖር ሲባል የተቀረጸ ብቻ ሳይሆን፤ ያንን የመድልኦ ስርአት በሰላማዊ መንገድ ለመለወጥ እንዳይቻል በሩን የዘጋም ጭምር ነበር። ከዚህ ካለፈ ደግሞ፤ አስፈላጊ ሁኖ ሲገኝ ህግ የማይመለከታቸው የጸጥታ ተቋማት ያሻቸውን አፈና እና ጭፍጨፋ ለማድረግ ፈቃዱ የነበራቸው ናቸው። እኒህ ሁለት የአገዛዙ ዘርፎች በመጨረሻ የሚቋጠሩት እና የሚተሳሰሩት ደግሞ፤ ደቡብ አፍሪካን ያሽከረክር በነበረው የናሽናሊስት ፓርቲው መሪዎች ዙሪያ ነበር።

አሜሪካ እና እንግሊዝን ደቡብ አፍሪቃ ውስጥ እንደነበሩ ትተን፤ ቦታን (Botha) በመለስ፤ ናሺናሊስት ፓርቲውን በወያኔ፤ የደቡብ አፍሪካን ጸጥታ ሀይል በአግአዚ ጦር፤ ፍርድ ቤቱን በመንበረ ጸሀይ ተክተን፤ ከላይ ያስቀመጥነውን የደቡብ አፍሪካ ሁኔታ ብናነበው፤ ከአሁኑ የኢትዮጵያ ሁኔታ የሚለይበትን አንዲት ነጥብ ማግኘት አዳጋች ይሆናል። በመሆኑም፤ የደቡብ አፍሪካ ችግር በመጨረሻው ላይ በሰላማዊ መንገድ ቢፈታም፤ እዚያ ለመድረስ ግን ብዙ ጠመዝማዛ መንገዶች እንደተጓዙ በማመላከት አግባብ ያለውን ትምህርት መቅሰም ተገቢ ይሆናል።

እንግዲህ ከላይ ከተቀመጠው አጭር ዳሰሳ መረዳት እንደምንችለው፤ ሰላማዊ ትግልን ስኬታማ ለማድረግ ታጋዮቹ ለሰላማዊ ትግል ያላቸው ጭፍን እምነት ብቻውን በቂ አይሆንም። ይህ ጭፍን እምነት በተለይ በሌሎች ሃገሮች የታየውንና የተሰራውን በሙሉ በሃገራችን ተጨባጭ ሁኔታ ውስጥ እንደሚሰራ አድርጎ ከሚያቀርብ አመለካከት ጋር ከተያያዘ ደግሞ አደገኛ ነው። በአለማችን ዴሞክራሲያዊ ስርአት ለመመስረት የቻሉት አብዛኛዎቹ ሀገሮች በአመጽ የተደገፈ እንቅስቃሴ ያደረጉ እንደነበሩ እየታወቀ በሃገራችን የሰላማዊ ትግሉ መሄጃ ባጣበት ሁኔታ ሌላ አይነት የትግል ስልት አማራጭ ማሰብ የዴሞክራሲያዊ ትግሉን ፈር የሚያስት ነው የሚል የተሳሳተ ክርክር ሌላው ቢቀር ለምሁራዊ ተአማኝነት ሲባል በፍጥነት መታረም ይኖርበታል። በሌላ በኩልም ሰላማዊ በሆነ የህዝብ ትግል የስልጣን ሽግግር የተደረገባቸው አንዳንድ የምስራቅ አውሮፓና የአፍሪቃ ሀገሮች ወደ አምባገነናዊነት ሲንሸራቱቱ አይተናል።

ህዝብ በዴሞክራሲያዊ መንገድ ለስልጣን ያበቃቸው መሪዎችና ፓርቲዎች መብቱን እየገፈፉት ከፍተኛ የእልቂትና የብጥብጥ ድግስ ሊደግሱለት እንደሚችሉ ዩክሬን፣ ጆርጂያና ኬንያ የመሳሰሉት ሃገሮች ጥሩ ምሳሌዎች ናቸው። ይህንን እያወቁ በሰላማዊ ትግል የሚፈጠር የስልጣን ሽግግር ብቻ የአምባገነንነት ማሳረጊያ እንደሚሆን ተደርጎ የሚቀርበው አሳቻ ገለጻ ሌላው መታረም ያለበት ጉዳይ ነው። የዴሞክራሲ ትግልን የተሳካ የሚያደርጉት ጉዳዮች በትግል ስልት ላይ ብቻ የሚሽከረከሩ አይደሉም። ከሰልጣን በፊት ለስልጣን አያያዙ ሂደት፣ ከስልጣን በፊት የስልጣን ብልግናን ለመካከል ለሚችሉ ነጻ ተቋማት፣ ከስልጣን በፊት በህዝብ ድምጽ ከሰልጣን መወገድ የዴሞክራሲ እምነት መሰረት መሆኑን የተረዱ የፖለቲካ ራእይና ጽናት ያለቸው፣ የሚገነቡት ፍትሃዊ የበለጸገና የተከበረ ሃገርና ህብረተሰብ የግልና የታሪክ ሽልማታቸው መሆኑን አስቀድመው ማየት የሚችሉ መሪዎችና በዴሞክራሲ እሴቶች ዙረያ የገነቡት የፖለቲካ ድርጅተና ያስተባበሩት ህዝብ ይጠይቃል። በሰላም ተመጣም በጠመንጃ ይህን ጸጋ የተላበሰ እንቅስቀሴ ካለተፈጠረ ከሌለ የአንድን ህዝብ ውብ ህልም ወደ አስፈሪ ቅዠት ለመቀየር አስቸጋሪ አይደለም።

ከእዚህ በተጨማሪ ግልጽ መሆን ያለበት ጉዳይ ሰላማዊ ትግል ከአመጽ ትግል የማይተናነስ የአላማ ጽናት፣ ወኔ የሚጠይቅ፣ ከፍተኛ በሆነ መስዋእትነት የተሞላ የትግል ሰልት መሆኑን ነው። ይህንን የትግል ስልት በስራ ላይ ለማዋል የትግሉ መሪዎች የህዝብን ነባር የችግር አፈታት ባህልና አመለካከት የሚቀይር አጅግ ፈታኝ ስራ እንደሚጠይቃቸው መታወቅ አለበት። እራሳቸው የህዝብ መሪዎች ካደጉበትንና ከኖሩበት አመጽን የልዩነት መፍቻ አድርጎ ከሚያየው ባህል ራሳቸውን በቅድሚያ ማጠብና ማንጻት አለባቸው። ሰላማዊ ትግል ራስን ከቂም በቀል አጽድቶ ባላንጣን ሳይቀር ከህሊናው ጋር እንዲታረቅና በሚፈጠረው በጎ ሁኔታ ተጠቃሚ እንዲሆን ሳይታክቱ የሚያሰራ የግል ህሊና ይጠይቃል።

ሰላማዊ ትግል እልቂት የማይኖርበት፣ ሰው የማይታሰርበት፣ ሰው ንብረቱን ነጻነቱን የማይገፈፍበት፣ ከቀየው የማይፈናቀልበት የፈሪዎችና የወኔ-ቢሶች የትግል ስልት አይደለም። እንዲያውም የሰላመዊ ትግል ስልት ከደፋሮችም በላይ ደፋሮችን የሚጠይቅ በመሆኑ ጠመንጃ ከማንሳቱ የከበደ እንጂ የቀለለ አይደለም። የሰለማዊ ትግል ስልት መሃንዲስ ጋንዲ ያለውን ማስታወሱ አግባብነት አለው። ጋንዲ "ፍራቻ ከሆነ ሰላማዊ ትግል የሚያስመርጠን ጠመንጃ አንስተን ብንወጋ ይሻልል" ብሎ ነበር። ይህን ያለበት ምክንያት የሰላማዊ ትግል ተከታዮች ትልቁ ጥንካሬ ለሞት ያላቸው ንቀት ነው። ገዳዮቻቸውንም ጭምር የሚያሸብረው ህሊና እንዲገዙ የሚያስገድዳቸው ይህ ለሞት የተሰጠ ንቀት ነው ብሎ ሰለሚያምን ነው። ሰላማዊ ታጋዩ በሰውነቱ በዜግነቱ ይገባኛል የሚላቸውን መብቶቹ እንዲከበሩለት ለማድረግ ሲነሳ የሚፈራው ምንም ነገር የለም።

ሰላማዊ ትግል ስልጣን ላይ ያለውን ጨቋኝ በመለምን፣ በመማላድ፣ የጠየቀውን በመስጠት፣ ሲ.ጋፋ መንገድ በመልቀቅ የሚከናወን አይደለም። አልፎ አልፎ ጨቋኞች ህሊና እንዲገዙ ልመናና ምልጃ ሊቀርብ ይችላል። ሰለማዊ ታገዩ ይህን በማድረግም ውርደትና ሃፍረት አይሰማውም። ይህ ምልጃና ልመና ግን በከፍተኛ ሰብአዊ ክብርና ደፋርነት ጋር የተያያዘ እንጂ ሰብአዊ ክብርን ባስነጠቀ አወራጅ ሁኔታ የሚፈጸም አይደለም። ሰለማዊ ትግል ፍተሃዊ አቋም ይዞ አልነቃነቅም፤ አልታዘዝዝም፤ አላደርግም በሚል እምቢተኛነት ከባላንጣ የሚመጣን ማንኛውንም ቅጣት፣ ሞትንም ቢሆን ለመቀበል ያመኑ መሪዎችና እነዚህ መሪዎች ያስተማሩት የሚያምናቸውና በስፋት ሊያንቀሳቅሱት የሚችል ህዝብና ይህ ህዝብ ሰላማዊ በሆነ መንገድ ሊንቀሳቀስ የሚችልበት አጠቃላይ ሁኔታ ሲኖር ብቻ የሚከናወን ነው። ሰላማዊ ትግል የባላንጣን ደም ለማፍሰስ ፍለጎት

የሌለው፣ ነገር ግን የራስን ደም በመስዋእትነት በመገበር የሚደረግ፣ ከወታደራዊ ትንንቅ የማይተናነስ የራሱ የስትራተጂና የታክቲክ ስልቶችና ዝግጅቶች የሚጠይቅ ጥበብ ያለው ነው። የሰላማዊ ትግል ውሎ አድሮ የሚተማመነው በሁለት ነጥቦች ላይ ነው። አንዱ ትግሉ ያነሳቸውን ፍትሃዊ ጥያቄዎች ደግፎ በሚነቃነቀው የማያቋርጥ የህዝብ ድጋፍና ለሰላመዊ ትግል በሚከፈለው የመስዋእትነት ዝግጁነት ላይ ነው። ሌላው ትልቁና ገዥው ቁምነገር የትግሉ ባላንጣዎች እንደማንኛውም ሰው ህሊና ስላላቸው መልሶ አካለዊ ጥቃት የማይሰነዝርን ህዝብ ለዝንተአለም እየቀጠቀጡና እየገደሉ ለመቀጠል ህሊናቸው አይፈቅድላቸውም በሚል እምነት ላይ የተመሰረተ ነው።

ሰለማዊ ትግል ሲባል በሃገራችን እንደምናየው በወያኔ በጎ-ፈቃድና በወያኔ ህግ ተለጉሞ መንቀሳቀስ ማለት አይደለም። ይህ ሰላማዊ ትግል ሳይሆን በቀጥታ ከወያኔ በሚገኙ ጥቅሞች ወይም በሌሎች ምክንያቶች የወያኔ የግፍ ስርአት ለማጀብ መሰለፍ ማለት ነው። ምንም ማድረግ በማይቻልበት በወያኔ ፓርላማ ገብቶ መቀመጥ ወይም ለመግባት መቁነጥነጥ የወያኔ ደሞዝና ጥቀማጥቅም እየተቀበለ ከሚኖረው የመንግስት ተቀጣሪ ከሆነው ግለሰብ የሚለየው የለም። ልዩነት ቢኖር የመንግስት ተቀጣሪው እራሱን የነጻነት ታጋይ አድርጎ እራሱን የማይሸነግል ህዘብንም የማይደልል መሆኑ ላይ ነው።

ሌላው መሰረታዊ ቁም ነገር ሰላማዊ ትግል ከአንድ ሃገር የፖለቲካ የኢኮኖሚ የባህልና የታሪክ ማእቀፍ ውጭ፣ ከአንድ ሃገር ነባራዊና ተጨባጭ ሁኔታ ውጭ በምኞት የሚሆን አይደለም። በተቃዋሚ ፓርቲዎች በተለይ በቅንጅት ውስጥ፣ በደጋፊዎቹና በአጠቃላይ በህዝቡ ውስጥ ከእዚህ በላይ ባነሳናቸው የሰላማዊ ትግል መሰረታዊ ነጥቦች ዙሪያ የነበረው ግንዛቤ እዚህ ግባ የሚባል እንዳልነበር ብዙ መረጃ ማቅረብ አያስፈልግም። ለእዚህ ነው ሰለማዊ የትግል ሰልት በኢትዮጵያ ሁኔታ በአጋጣሚ የተወደቀበት ወይስ በበቂ ግንዛቤ ላይ ተቁሞ የተደረገ ምርጫ የሚል ጥያቄ ቀደም ብለን እንድናነሳ የተገደድነው። በቅንጅት ውስጥ ጥቂት ሰዎች ስለሰላማዊ ትግል ምንነት መጽሃፍ ስላነበቡ፣ በርከት ያሉት ደግሞ በአለማችን በታሪክ የታወቁ የሰላማዊ ትግል አርበኞችን ዝነኛ ንግግሮችና ጽሁፎች መጥቀስ መቻላቸው፣ ሰላማዊ ትግል የተደረገባቸውን ሃገሮች ስም በምርጫ 97 የክርክር ወቅት በመጥራታቸው፣ በሃገራችን ውስጥ መደረግ ስለሚገባው የሰላማዊ ትግል በቂ እውቀትና ዝግጅት ነበር ማለት አይደለም።

ከሁሉም በላይ ግን አሁንም ትልቅ ችግር ያለው የሰላማዊ ትግሉ በላንጣ የሆነውን የወያኔን ምንነት ለራስ ፍለጎቶች ሲሉ በሚገባ ለመመርምር አለመፈለጉ ላይ ነው። ቀደም ብለን እንደጠቀስነው ዛሬ በሃገራችን የነገሰው የወያኔ አገዛዝ፣ ህንድን በቅኝነት ከያዘው የእንግሊዝ አገዛዝ ወይም በምስራቅ አውሮፓ ከነበሩት አገዛዞች ወይም ማርቲን ሉተር ኪንግ ለጥቁር መብት ለመታገል ከተነሰባት አሜሪካ አስተዳደር ጋር ምንም የሚያገናኘው ነገር የለም። በተጠቀሱት ሃገሮች ሰላማዊ ትግል ለማድረግ ያስቻሉ ሁኔታዎች ነጻ በምንላት ሀገራችን ፈጽሞ የሌሉ መሆናቸውን ቀደም ብለን ለማስገንዘብ ሞክረናል። በእነዚህ ሃገሮች የተደረገውን ትግል በምሳሌነት በመጥቀስ የፈለግነውን ያህል ብናነበንብ የሃገራችንን ተጨባጭ ሁኔታ አይቀይረውም። ‹ታንጎ ለመደነስ ሁለት ሰው ያስፈልጋል› እንዲሉ ሁሉ፤ ሰላማዊ ትግልን እውናዊ በሆነ ሁኔታ ለማካሄድ፤ ከታጋዮች የእምነት ጽናት በተጨማሪ በስልጣን ላይ ያለው ወገን ባህርይም ወሳኝነት አለው። የጋንዲን የህይወት ታሪክ የጻፈቸው የጋንዲ አድናቂ የነበረችው ወይዘሮ ሮቤርታ *(Roberta Strauss Feuerlicht)* እንዳለቸው የጋንዲ የሰላማዊ ትግል እንዲሰራ ባለንጣችን የሰለጠነ መሆን አለበት። ወይዘሮዋ፤

> "ጋንዲ ከምገድል ብገደል ይሻለኛል በሚልበት ወቅት አዶልፍ ሂትለር የሁለተኛውን
> የአለም ጦርነት አቀጣጠለው። ይሁዲዎችንም ከምድረ-ገጽ ለማጥፋት እየሰበሰበ መፍጀት
> ጀመረ። በዚያን ጊዜ በእዚህ ጉዳይ ላይ የጋንዲ ምክር ሰላማዊ ትግል ማድረግና ራስን
> ለመስዋአትነት ማቅረብ የሚለው ነበር።
> አስፈላጊ ሆኖ ከተገኘ በመቶዎች ሳይሆን በሽዎች የሚቆጠሩ ሰዎች
> የአምባገነኖችን የደም ጥማት ለማርካት ለእርድ ሊቀርቡ ይገባል እስከማለት በእምነቱ ጸና።
> ጋንዲን ስላዳመጡ ሳይሆን በባህላቸው የተነሳ ይሁዲዎች የናዚዎችን ጭፍጨፋ ያለምንም የአመጽ
> ተቃወሞ ተቀበሉት። ጋንዲ እንዳለው መቶዎችና ሽዎች ብቻ ሳይሆኑ ከስድስት ሚሊዮኖች
> በላይ የሚሆኑ ተጨፈጨፉ። ጭፍጨፋው ያበቃው ናዚዎችን በአመጽ የደመሰሰ
> ሃይል በምምጣቱ እንጂ ይሁዳውያኑ በሰላም ለማለቅ ዝግጁ ስለነበሩ
> አይደለም። ከናዚዎች መምጣት በፊት የጋንዲ የሰላማዊ እምቢተኛነት የትግል

> ስልት ፍቱን የትግል መሳሪያ መሆኑ ቢረጋገጥም፣ ፍቱን መሳሪያ መሆን የሚችለው ባላንጣዎቻችን የሰለጠኑ ሲሆኑ ብቻ እንደሆነ ናዚዎች አረጋግጠውታል።"[21]

ታጋዮች ለሰላማዊ ትግል ያላቸው እምነት ጽናት የሚለካው፤ ሁኔታው በማይፈቅድበት ወቅት በቀኖናዊነት በመቆም ሳይሆን፤ ሰላማዊ የሆነ ትግል የሚያስችል ሁኔታ እንዲፈጠር የሚያስችሉ አግባብነት ያላቸውን የትግል ስልቶች በመቀረጽ እና ሁኔታው ሲፈጠር ደግሞ ሰላማዊ የትግል ስልትን በተግባር ለማዋል ዝግጁ በመሆናቸው ይኖርበታል።

ስለዚህ፤ በአሁኑ ወቅት በሀገራችን ውስጥ ሰላማዊ ትግልን ለማካሄድ የሚያስችል ሁኔታ አለመኖሩን ቀደም ብለን እንዳሳየን በማስታወስ፤ ሊነሳ የሚችለው አግባብነት ያለው ጥያቄ "ሰላማዊ ትግልን ለማካሄድ የሚያስችል ሁኔታን እንዴት መፍጠር እንችላለን? ወይም ሰላማዊ ትግል ሊካሄድ የሚችልበትን ሁኔታ ለማስከተል ምን አይነት የትግል ስልት መቀረጽ ይኖርበታል?" የሚለው ብቻ ይሆናል።

በእኛ እምነት፤ ሰላማዊ እና ህጋዊ ትግል ሊጓዙ የሚችሉበት ድረስ ሂደው የተወሰኑ ድሎችን አስመዝግበው አብቅተዋል። ሰላማዊ ትግል በጠላት ላይ የሞራል የበላይነትን በገሀድ እያረጋገጡ በማስመዝገብ የሚገፋ በመሆኑ፤ ትግሉ በሚካሄድበት ሃገር ውስጥ የህግ የበላይነት መስፈንን እንደ ቅድመ ሁኔታ የሚጠይቅ ነው። ህግ በሌለበት ሀገር ውስጥ ህጋዊና ሰላማዊ ትግል አካሂዳለሁ ብሎ ማሰብ ስለማይቻል ግን፤ የሰላማዊ ትግል ጥያቄ እዚያው ላይ የሚያቆም ይሆናል። ስለዚህ፤ ዋነኛውን የወቅቱን የትግል ስልት ስናጤንም፤ ሰላምን አጥብቀን ብናፈቅራትም፤ ምኞትን ትተን እውናዊ አመለካከትን መያዝ ያስፈልጋል።

ስለዚህ፤ በእኛ አስተያየት፤ ከላይ ያስቀመጥነው ጥያቄ መልስ ደቡብ አፍሪካውያን ተመሳሳይ ሁኔታ ሲያጋጥማቸው የወሰዱት የ‹አመጽ› መንገድ ብቻ ነው። ምክንያቱም፤ ቀደም ብለን እንዳሳየነው ከአመጽ ውጭ ወያኔ ለሰላማዊ ትግል በሩን እንዲከፍት ሊገፋው[22] የሚችል ሌላ ምንም አይነት ሁኔታ በአሁኑ ወቅት የማይታይ በመሆኑ ነው።

<u>ማሳረጊያ</u>

ይህንን ጽሁፍ በጨለምተኛነት ላለመደምደም፤ ከመሳሪያ ትግል ስለሚከተል ሰላማዊ ትግል ያለንን ተስፋ የደቡብ አፍሪካን ሁኔታ በጥቂቱ በማስታወስ እናጠቃልላለን። የአፍሪካ ናሽናል ኮንግሬስ አርበኞች አቶሚክ ቦንብ የታጠቀውን መንግስት የገጠሙት የነፍስ ወከፍ መሳሪያ ታጥቀው ነበር። ወታደራዊ እብሪተኞች የመሳሪያ አቅምን በማወዳደር ብቻ፤ እንዲህ አይነቱ ሙከራ የትም እንደማይደርስ አስበው ሊሆን ይችላል። እብሪተኞቹ ያልተረዱት ጉዳይ ግን፤ የእንዲህ አይነቱ ትግል መሰረት የሆነው፤ በደልን ከመቀበል ሞትን የመምረጥ ጽናት፣ በቀጥታ የሚጋጨው ግኡዝ ከሆነው የጨቋኞች የጦር መሳሪያ ጋር ሳይሆን ከራሳቸው ከጨቋኞቹና ከደጋፊዎቻቸው ህሊና እና ይብዛም ይነስም ከተላበሱት ስብእና ጋር ነው። የታፈነ ህዝብ ለነጻነቱ የሚሳየው ጽናት ብዙ ዳር የቆሙ አጋዦችን ለትግሉ ሲያበረክት፤ ጨቋኞችን ደግሞ ማለቂያ የሌለው ወታደራዊ ጉልበታቸውን እንደታቀፉ ይፈረካክሳቸዋል[23]። በደቡብ አፍሪካ የሆነውም ይህ ነው።

ጨቋኞች እና አጃቢዎቻቸው በፍትሀዊ ጦርነት ፊት አንድነታቸውን ጠብቀው ሊጓዙ አይችሉም። የጨቋኞች አንድነት ፈተና በሌለበት ሁኔታ ውስጥ አልባሌ በሆኑ ጥቅሞች አስተሳሳሪነት የተገነባ ነው። ህሊናቸውን እና ነፍሳቸውን በጥልቀት የሚፈትን ነገር ሲመጣ ያስተሳሰራቸው ክር ሁሉ መበጣጠስ ይጀምራል። በዚያውም መጠን የመከላከል አቅማቸው ይደክማል፤ ወኔያቸው ይላሽቃል። በአንጻሩ ደግሞ፤ የፍትህ ታጋዮች መንፈስ

---

[21] Gandhi: a concise biography Roberta Strauss Feuerlicht. New York, American R.D.M. Corp. c1965

[22] ካለፉት ሁለት አመታት ልምዳችን ልንማር እንደቻልነው፤ ይህንን መንግስት በመግፋት አስተዋጽኦ ሊያደርግ ይችል የነበረው የምእራብ መንግስታት ተጽእኖ ምንም ተስፋ ሊጣልበት የማይችል ነው። ይህ ተጽእኖ ራሱ እንዲመጣ ለማድረግም፤ አመጽ አስፈላጊ ሁኖ ይታያል።

[23] የሰው ልጅ በተፈጥሮው ጥሩ ሳይሆን ይቀራል? ለዚህስ ይሆን በግብዝነት ታፍኖ የተያዘ ህሊና፤ ለፍትህ እና ርትእ ጽናት ባለው መንፈስ ሲመታ ብትንትኑ የሚወጣ? ታዲያ አመጽ የወያኔ መኳንንትን ከህዝባቸው የሚቀላቅላቸው ንስሀ ይሆንልን ይሆን?

ይበረታል። በመጨረሻም በደቡብ አፍሪካ እንደሆነው ሁሉ፤ ሰላማዊ ትግልን ለማኬድ የሚያስችል መድረክን እንዲቀበሉ ሊገደዱ ይችሉ ይሆናል።

ለእንዲህ አይነቱ ውጤት ግን አመጽ ብቻውን በቂ አይደለም። የአመጹ የፖለቲካ ግብ፣ ቅርጽ እና አካሄድ እኩል ወሳኝነት ያላቸው ጉዳዮች ናቸው። ምን ጊዜም ቢሆን፤ የአመጽን መንገድ የመረጥነው ወድደን ሳይሆን ተገድደን መሆኑን እና አመጽን ነቅፈን ሰላማዊ መንገድን የወሰድን ጊዜ የደረደርናቸው የሰላማዊ ትግል እሴቶች/ጸጋዎች አለመለወጣቸውን ማስታወስ ይኖርብናል። አመጽ የራሱ የሆነ ዳይናሚክስ ስላለው፤ በዚያ አዙሪቱ ውስጥ እንዳይከትተን ተጠንቅቀን መሄድ አለብን። አመጹ ከጥላቻ ነጻ የሆነ፤ ፍትህን በምንም መልኩ የማያጣጥል፤ ራሳችንን እንደጠላቶቻችን ሁሉ የስሜታችን ባሪያ የማያደርገን፤ ጨቋኞቹ ህሊናቸውን እንዲዘጉ እድል የማይሰጣቸው መሆንም ይኖርበታል።

በመሆኑም፤ ይህ የአመጽ ትግል የሚኖረው ቅርጽ እና አካሄድ በጥንቃቄ መጠናት አለበት። በሚቀጥለው ምእራፍ የምናተኩርበትም ጉዳይ ይኸው ይሆናል።

ጸሃፊዎች
በእምነቱ ዘለቀ
አንዳርጋቸው ጽጌ          የካቲት 2000

**<u>የጸሃፊዎቹ ማስታወሻ</u>**

የእጽሁፉ አለማ አደጋኛ አጣብቂኝ ውስጥ የወደቀውን በሃገራችን ተጀምሮ የነበረውን የዴሞክራሲ ትግል ከገባባት አጣብቂኝ የሚያወጣውን ሃሰብ ለመሰንዘር። ይህን ጸሁፍ ለማሳጠር ሲባል ወደ ፊት በሚገባ መተንትን የሚገባቸውን ጉዳዮች በጥቅሉ ብቻ ያካተተ መሆኑን እናውቃለን። በበኩላችን ግን መሰረታዊ ባልናቸው ጥያቄዎች ላይ ጽሁፉ ግልጽ አቋም እንዲወስድ አድርገናል። የተወሰደውን አቋም መተቸት አንዱ የውይይት አግባብ ቢሆንም እንዲጀመር የምንፈልገውን ውይይት የበለጠ የሚያዳብረው ከእዚህ ጽሁፍ የተለየ የሃገራችንን የፖለቲካ ሁኔታ የሚገመግሙና መፍትሄውንም የሚጠቁሙ ሃሰቦች አሉን የሚሉ ግለሰቦች የራሳቸውን ሃሰቦች ጥርት አድርገው በጽሁፍ ሲያስቀምጡ ነው ብለን እናምናለን። በመሆኑም የሃገራችን የተቃዋሚ የፖለቲካ ድርጅቶች መሪዎችና ምሁራን በእንደዚህ አይነቱ ጽሁፍ ላይ እንዲያተኩሩ ጥሪያችንን እናቀርባለን። ጽሁፎቹንም አብዛኛው የሃገራችን ህዝብ በሚያነበው የአማርኛ ቋንቋ ማድረጉ ወይይቱን በዋንኛነት ጉዳዩ ወደሚመለከተው የሃገራችን ህዝብ ለማድረስ ይረዳልና በተቻለ መጠን በአማርኛ ቋንቋ ይጻፉ እንላለን። በእንግሊዝኛም የሚጻፍ ከሆነ የአማርኛ ትርጉሙ አብሮ እንዲወጣ ጥረት ማድረግ ተገቢ ይሆናል። በሃገር ቤት የማሰራጨቱን ስራ ህዝቡ እራሱ ስለሚሰራው በስርጨት ስለሚኖረው ችግር መጨነቅ አይኖርብንም።